## መግቢያ፡-

በዩኒቨርስቲ ውስጥ በሥነ-ምግባር የታነጹ ተማሪዎችን ለማፍራት እና መልካም ሥነ-ምግባር በማስፈን ዉጤታማ ሥራ እንዲሰራ ለማስቻል ተማሪዎች የግድ የስነ-ምግባር ደንቦችን በሚገባ አዉቀዉና ተረድተዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ በማድረግ  በመልካም ሥነ-ምግባር ተገንብተዉ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም/ሌላው ጉዳይ ደግሞ በዩኒቨርስቲው ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ወይም የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞች እውቀታቸውን እና ችሎታቸውን ለተቀጠሩበት መሥሪያ ቤት በአግባቡ ትክክለኛ አገልግሎት እንዲሰጡ እና ጥፋት ፈጽመው ስገኙ በአመለካከታቸው እና በሥነ-ምግባር ታርመው ብቁ ሠራተኛ ለማድርግ በአዋጅ እና በደንብ የተደነገጉ የዲስፕሊን እርምቶችን መስገንዘብ ተፈልጎዋል፡፡

በመሆኑም ይህ መጽሔት/Booklet በሦስት ምዕራፎች ተከፍሎ ቀርቧል ፡፡ ምዕራፍ አንድ በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ በ2006 ዓ/ም ተዘጋጅቷ የጸደቀ የተማሪዎች ሥነ-ምግባር መመሪያ ደንብ ስሆኑ በውስጡ ስለሥነ-ምግባርና በሥነ-ምግባር ጉድለቶች ምክንያቶች እንደ ጥፋተቸው መጠን በተማሪዎች ላይ የሚወሰደው የዲስፕሊን ቅጣት ዓይነቶች ይዞዋል፡፡ ምዕራፍ ሁለት በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 እና በፌደራል መንግስት ሠራተኞች የዲስፕሊን አፈጻጸምና ቅሬታ አቀራራብ ሥነ-ሥርዓት ደንብ 77/1994 ላይ ከሠራተኛ ሥነ-ምግባር እና የዲስፕሊን  ቅጣት ዓይነቶች ጋር ተያይዞ ለሠራተኞች ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በአጭሩ ቀርቧል፡፡ ምዕራፍ ሦስት በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ተዘጋጅቷ በ2003 ዓ/ም የጸደቀ የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞች የሥነ-ምግባር መመሪያ ስሆኑ በውስጡ ስለሥነ-ምግባርና በሥነ-ምግባር ጉድለቶች ምክንያቶች እንደ ጥፋተቸው መጠን በአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞች ላይ የሚወሰደው የዲስፕሊን ቅጣት ዓይነቶች ይዞዋል፡፡

በተለይም/በተጨማሪ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች እና የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞች የፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 እና የፌደራል መንግስት ሠራተኞች የዲስፕሊን አፈጻጸምና ቅሬታ አቀራራብ ሥነ-ሥርዓት ደንብ 77/1994 ሙሉ በሙሉ አንቢበው ከሠራተኛ ጋር ተያያዥ በሆኑ ሌሎች ጉዳዮችን ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ እንገልጻለን፡፡

ተጨማሪ መረጃ መግኘት እንደሚቻል ማሰሳብ

# ምዕራፍ አንድ

# የተማሪዎች ሥነ-ምግባር መመሪያ ደንብ

## ክፍል አንድ፡- የተማሪዎች ሥነ-ምግባር ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1፡- አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 001 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

**አንቀጽ 2 ትርጓሜ፡-** የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1 «**ተማሪ**»፡- **ማለት** በዩኒቨርሲቲው በመደበኛና በተከታታይ ፕሮግራም ለመማር የተመዘገበና የታደሰ የዩኒቨርሲቲው የተማሪ መታወቂያ ካርድ ያለዉ ሰዉ ነዉ፡፡

2.2 «**ቅጥር ግቢ**»፡- ማለት በዩኒቨርሲቲው በባለቤትነት በተያዘዉ ክልልና ቅርንጫፍ ት/ቤቶችና የምርምር ሥፍራዎችን ጨምሮ ነዉ፡፡ ሆኖም በዩኒቨርሲቲው የቀን፤የማታ፤ የተከታታይ ትምህርት፤ የማስተማር ልምምድና ጉዞዎች በሚካሄድባቸው ቦታዎች ሁሉ መመሪያው ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

2.3 «**ዩኒቨርሲቲ**»፡- ማለት የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡

2.4 «**ማናጅመንት ቦርድ**»፡- ማለት በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው፡፡

2.5 **«ፕሬዚዳንት»** ፡- ማለት በዚህ መመሪያ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንትን የሚመለከት ነው፡፡

2.6 «**የዩኒቨርሲቲው የተማሪ የዲስፕሊን ኮሚቴ**»፡- ማለት በዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሚቋቋምና ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንት ሆኖ በስነ-ምግባር ጉድለት የሚከሰሰዉን ወይም የምትከሰሰዋን ተማሪ ጉዳይ እየመረመረ የዉሳኔ አስተያየት ለዩኒቨርስቲዉ ፕሬዚዳንት የሚያቀርብ አካል ነው፡፡

2.7 «**ቋሚ አባላት**»፡- ማለት ከሚመለከታቸዉ የሥራ ክፍሎችና ከተማሪዎች ህብረት የሚወከሉ የዩኒቨርሲቲው የተማሪ የዲስፕሊን ኮሚቴ አባላት ማለት ነው፡፡

2.8 «**ተለዋጭ አባላት**»:- ማለት ከዩኒቨርሲቲው አካዳሚክና አስተዳደር ዘርፎች በጥመረት ተወክለው እንደየአስፈላጊነቱ የሚሳተፉ የተማሪ የዲስፕሊን ኮሚቴ አባላት ማለት ነው፡፡

2.9 «**ደህንነት**»:- ማለት በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ውስጥ የማንኛዉም የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ሰብአዊ፣ ህጋዊና አካዳሚያዊ መብት መከበር ማለት ነው፡፡

2.10 «**አንድ ወሰነ ትምህርት**»:- ማለት በደንቡ መሰረት አንድ ሴሚስተር የትምህርት ጊዜ ማለት ነው፡፡

2.11 «**ማሕበራዊ አገልግሎት**»:- ማለት በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት ሆነው የተማሪውን አቅም ያገናዘቡ ስራዎች ማለትም በተማሪዎች መመገቢያ አገልግሎት ውስጥ መመገቢያ ስሀን የመሰብሰብ፣የማጠብ፣ሻይ ለተማሪዎች መቅዳት፣በግቢ ማስዋብ አገልግሎት ውስጥ ችግኝ መትከል፣መንከባከብ፣ግቢ መጥረግ፣በላይብረሪ አገልግሎት ውስጥ መጽሀፍ ለተማሪዎች ማደል፣መሰብሰብ፣ መጽሀፍ መደርደርን ያካተተ ነው፡፡

**አንቀጽ 3 ፡-የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ የሥነ-ምግባር መመሪያ በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ 4 ፡- የፆታ አገላለጽ**:- በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለጸዉ የሴትንም ፆታ ያጠቃልላል፡፡

**አንቀጽ 5 ፡-የሥነ-ምግባር መመሪያ ዓላማ**

1. በሥነ-ምግባር የታነጸ ተማሪ ማፍራትና መልካም ሥነ-ምግባር በማስፈን ዉጤታማ ሥራ እንዲሰራ ማስቻል፡፡
2. የሥነ-ምግባር ጉድለቶች እንዳይፈፀሙ ማስገንዘብ ተፈጽመዉም ሲገኙ እርምጃ ለመዉሰድ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፡፡
3. ተማሪዎች የስነ-ምግባር ደንቦችን በሚገባ አዉቀዉና ተረድተዉ ተገቢዉን ጥንቃቄ በማድረግ በዩኒቨርስቲ ቆይታቸዉ በመልካም ሥነ-ምግባር ተገንብተዉ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
4. ተማሪዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸዉን ያለእንከን ሊመሩ ይቻላቸዉ ዘንድ
5. ስለሥነ-ምግባርና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ምንነት ተረድተዉ ከደንብና ሥርዓት ዉጭ በሚሆኑበት ጊዜ ሊወሰድባቸዉ ስለሚችል እርምጃ በቂ ግንዛቤ ሊጨብጡ ይገባቸዋል፡፡

**አንቀጽ 6. የተማሪዎች ኃላፊነትን በተመለከተ**

1. ተማሪዎች ይህንን የሥነ-ምግባር መመሪያ በሚገባ አዉቀዉ በተግባር ላይ ማዋል አለባቸው፡፡
2. ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ዉስጥ ከሥነ-ምግባር ጥሰት ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ሲፈጽሙ ለዩኒቨርሲቲዉ የበላይ ኃላፊ የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. ተማሪዎች ይህንን መመሪያ የመቀበልና የመፈጸም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>:- አጠቃላይ የሥነ-ምግባር መርሆችና የዲስፕሊን ጥፋቶች

**አንቀጽ 8. ቅንነት**

- **በቅንነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. የዩኒቨርሲቲዉን ክብርና ዝና የሚጎዳ፣ የተማሪዉንና የዩኒቨርሲቲዉን ማህበረሰብ የሚያዉክ ባህሪይና ተግባር መፈጸም ወይም ማሳየት፣

ለ.የዩኒቨርስቲዉን ህግና ደንብ በመጣስ ሱስ በሚያስይዝ መድሃኒት ወይም በአደንዛዥ እፅ ሱስ በመመረዝ ወይም በልማዳዊ መጠጥ ተጽእኖ ምክንያት ትም/ትን በአግባቡ አለመከታተልና ተገቢ ያልሆነ አድራጎት መፈጸም፣

ሐ. በግልና በማህበራዊ ህይወታቸዉ ዩኒቨርሲቲዉንና የዩኒቨርሲቲዉን ማህበረሰብ መልካም ግምትና አመኔታ የሚያሳጣ ድርጊት መፈጸም

መ. የተሳሳተ መረጃን በተለይም ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች በመስጠት ህገ-ወጥ ተግባራትን መፈጸም፡፡

**አንቀጽ 9 ግልፅነት**

❖ **በግልፅነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. ህጋዊ ለሆኑ ከዩኒቨርስቲዉና ከዩኒቨርስቲዉ ማህበረሰብ ለሚቀርብ ጥያቄ ግልጽ ምላሽ ወይም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን

ለ. የዩኒቨርስቲዉ የተማሪዎች መማክርትና የተለያዩ ክበባት ለሚያስተላልፉት ዉሳኔ ተገቢዉን ማብራሪያ ወይም ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን

ሐ. ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸዉ ለቀሩባቸዉና ለሚቀሩባቸዉ ቀናት ህጋዊና ግልጽ መረጃ ለሚመለከተዉ አካል አለማቅረብ

መ. ህጋዊና ግልጽ ባልሆኑ መንገዶች ወደ ግቢ መግባት ወይም መዉጣት ወይም ንብረት ማዉጣት ወይም ማስገባት

**አንቀጽ 10 ፡- ታማኝነት**

❖ **በታማኝነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. የሀገሪቱንና የዩኒቨርስቲዉን ህግና ደንብ አለማክበር

ለ. በዩኒቨርስቲው በተማሪዎች ወይም በሌላ አካል የሚደረግ ህገ-ወጥ እንቅስቃሴን እያወቁ በጊዜ አለማጋለጥ ወይም ተባባሪ መሆን፡

ሐ. በማንኛውም አጋጣሚ ከዩኒቨርስቲዉ የተረከቡትን ማንኛዉም ዓይነት ንብረት ወይም መገልገያ በጥንቃቄ አለመያዝና ማበላሸት፣

መ. የዩኒቨርስቲዉን ማህበረሰብ ንብረት መስረቅ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፣

ሠ. በዩኒቨርስቲዉ የሚገኙ ወይም የሚሰጡ የጋራ አገልግሎቶች እንደ ሻዉር፣ ሽንት ቤት፤ ቤተ- መጽሀፍት፣ ማደሪያ ዶሪም የመሳሰሉትንና ሌሎች አገልግሎትን በግል ወይም በቡድን መጠቀም ወይም ለመጠቀም መሞከር፡

ረ. የሌሎችን ስራ እንደራስ አድርጎ ማቅረብ ወይም ለማቅረብ ማሞከር ያስቀጣል፡፡

**አንቀጽ 11፡- ምስጢር ጠባቂነት**

❖ **በምስጢር ጠባቂነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. ተማሪዎች በትምህርት ቆይታቸዉ ከሙያቸዉ ጋር በተያያዘ መልኩ ወይም ከዩኒቨርስቲዉ ሥራ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚያዉቋቸዉን ሚስጢሮች አለመጠበቅና የዩኒቨርስቲዉን መልካም ስም ማጉደፍ ያስቀጣል፡፡

**አንቀጽ 12 ፡- ሐቀኝነት**

❖ **በሐቀኝነት** ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. የተለያዩ የማጭበርበር ወንጀሎችን መፈጸም ወይም ለመፈጸም ሙከራ ማድረግ፣ ለምሳሌ፣አስመስሎ መፈረም፣ህጋዊ የሆኑ ሠነዶችን መሠረዝ፣መደለዝና አስመስሎ መሥራት፣

ለ. ፈተናን መኮረጅ፣ማስኮረጅ፣ከደብተር ወይም ከወረቀት መገልበጥ ወይም መሥራት ወይም የፈተና ወረቀትን ደልዞ ወይም ጨምሮ ከመምህር በህገ ወጥ መንገድ ዉጤት ለማስቀየር መሞከር፣

ሐ. ጉቦ በመስጠት ዉጤትን ለማስቀየር መሞከር ፣

መ. በዩኒቨርስቲዉ ዉስጥ ለሚደረጉ ነገሮች በሀሰት መመስከር ፣

ሠ. በዩኒቨርስቲዉ ክሊኒክ መድሀኒቶችን ለሌላ ተግባር ማዋል፣

ረ. የዩኒቨርስቲዉን መታወቂያ ካርድ ወይም የአገልግሎት መለያ ካርድ ወይም መመገቢያ ካርድ ለሌላ ግለሰብ አሳልፎ መስጠት

**አንቀጽ 13፡- ህግን ማክበር**

❖ በህግን ማክበር ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ በዩኒቨርስቲዉ የሚወጡ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን አለማክበርና አለመከታተል፡፡

ለ.በዩኒቨርስቲዉ ውስጥ ስልጣን ባለዉ አካል የሚወጡ ልዩ ልዩ ደንቦችን ለምሳሌ እንደ ቤተ-መጽሐፍ ቤተ-ሙከራ የተማሪዎች ማደሪያ (ዶርም ) እና ሌሎች ደንቦችን በቸልተኝነት ሆን ብሎ መጣስ፣

ሐ. በህጋዊ መልኩ የተባረረዉን ተማሪ በግቢዉ ውስጥ ማስጠጋት ወይም ማኖር ወይም ማሳደር

መ. ህጋዊ ያልሆኑ ጽሑፎችን በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ መበተን ወይም ማሰራጨት፣

ሠ. ማንኛዉም ተማሪ ማሟላት የሚገባዉን ነገር አልተደረገልኝም ብሎ ሲያስብ በግል ወይም በተወካዩ አማካይነት በህጋዊ መንገድ ማቅረብና ምላሽ ማግኘት ሲገባዉ ራሱንም ሆነ ሌሎችን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለአመጽ ማነሳሳት፣

ረ. በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ያልተፈቀደ ስብሰባ ማካሄድ፣አድማ ማሳደም፣ለማሳደም መሞከር፣ህገ-ወጥ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ወይም ለማድረግ መሞከር፣

**አንቀጽ 14፡- አርአያነት**

- ❖ በአርአያነት ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ/ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸዉ በመልካም ሥነ-ምግባር ግንባር ቀደም በመሆን የሚጠበቅባቸዉን መልካም አርአያነት አለማሳየት እና በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን መርሆች አለማክበር ወይም መጣስ፣

ለ/ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸዉ የዩኒቨርስቲዉ ስምና ክብር የሚያቀል መተማመንና መልካም አንድነት የሚያጠፋ ተግባርና እንቅስቃሴ ላይ መሰማራት፣

ሐ/ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸዉ ኢዴሞክራሲያዊ የሆነ እና በሀይልና በጉልበት ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን ከዩኒቨርስቲዉ ማህበረሰብ ጋር መመስረት፣

**አንቀጽ 15፡- ተጠያቂነት**

- ❖ በተጠያቂነት ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. ለግጭት የሚገፋፋና አሰነዋሪ የሆኑ ነገሮችን በቃል ወይም በጽሁፍ በመማሪያ ፣በመኖሪያ፣በመጸዳጃ፣በቢሮዎች ግድግዳዎች፣በመዝጊያዎች፤ በመስኮቶችና በቁም ሳጥኖች ላይ መጻፊ፣ስዕል መሳል ወ.ዘ.ተ.ያስቀጣል፡፡

ለ. ሥር የሰደደ የጥላቻ ባህሪይ በዩኒቨርስቲዉ ማህበረሰብና በአካዳሚክ ስታፍ ላይ ማሳየት ወይም ማንጸባረቅ፡፡

ሐ. የዩኒቨርስቲዉን ሠራተኞችና መምህራን መልካም ስም በሀሰት በጹሁፍ ወይም በሌላ መንገድ ሊያጎድፍ የሚችል ድርጊቶችን መፈጸም፡፡

መ. በመደራጀትና ረብሻን በማነሳሳት የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች እንዳይካሄዱ ማድረግና የዩኒቨርስቲዉን የስራ እንቅስቃሴ ማስተጎጎል፡፡

ሠ. በዩኒቨርስቲዉ ግቢ ዉስጥ በዘር፣በብሔር፣በፖለቲካ ልዩነት፣በሃይማኖት፤ በቀለም ክፍፍል ወ.ዘ.ተ. ፈጥሮ መሳደብ መደባደብና ግጭቶችን መፍጠር

ረ. በፈተና ወቅት ከወረቀት መስራትና ይህንን ሊያስቆሙ ከሚንቀሳቀሱ ፈታኝ መምህራን/ግለሰብ ጋር ግብግብ መፍጠር ወይም ለመደባደብ መሞከር

ሰ. በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ሴት ተማሪዎችን አስገድዶ መድፈር ወይም ለመድፈር ሙከራ ማድረግ፣

ሸ. ከዩኒቨርስቲዉ መምህራንና ሠራተኞች ጋር እንዲሁም እርስ በርስ ጥል ፈጥሮ መደባደብ፣መሳደብና ማንጓጠጥ፣

ቀ. በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ድምጽ ያለዉን ወይም የሌለዉን የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘትና ጉዳት ለማድረስ መሞከር

በ. ሴት ተማሪዎችን በንግግር፣ በጽሁፍ፣በኃይል ወ.ዘተ.ማስፈራራት፣ መዝለፍ፣ ማስቸገር ፣ማስጨነቅና ዉስባዊ ተንኮሣ ማካሄድ፣

ተ. የተማሪዉን ሥነ አእምሮ ሊጎዱ የሚችሉ ኃይለ-ቃሎችን በመጠቀም ( ለምሳሌ ሴት ተማሪዎችን ፣የአካል ጉዳትን፣የሰዉነት አቋምን፣ከባህል ጋር ግንኙነት ያላቸዉን ነገሮች ወዘተ) ምክንያት በማድረግ ተማሪዉ የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማዉ ማድረግ

ቸ. በመኝታ ክፍል ዉስጥ ምግብ ማብሰል፤ ሻይ ቡና ማፍላት፣ያልተፈቀዱ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ለምሳሌ ካዉያ ወዘተ መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት

ነ. የዩኒቨርስቲዉ የጋራ መገልገያ ቁሳቁሶችን ማበላሸት ለምሳሌ፣አልጋ፣መዝጊያ መስኮት፣በር፣የዉሃ ቧንቧዎችንና የሻዉር ዕቃዎችን መሰበርና ማበላሸት እንዲሁም የመጻህፍት ሰነዶችን መቅደድ እና መስረቅ

ኘ. የዩኒቨርስቲዉን ንጽህናና ጽዳት የሚጎዱ ድርጊቶች፣ለምሳሌ አበቦችን መንቀል አጥር ማፍረስ፣በዶርምና በመማሪያ ክፍሎች አካባቢ ሽንት መሽናት ወይም መፀዳዳት፣

አ. በተማሪዎች ማደሪያ፣በላይብረሪና በመማሪያ ክፍሎች አከባቢ ሌሎችን በሚያዉክ መልኩ ድምጽን ከፍ አድርጎ መጮህ ወይም መነጋገር፤

ከ. በዩኒቨረስቲዉ ግቢ ዉስጥ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ግልጽ የሆነ ወሲብ ሲፈጽሙ እጅ ከፍንጅ መያዝ

**አንቀጽ 16፡- ህጋዊ በሆነ ሥልጣን መገልገል**

❖ ህጋዊ በሆነ ሥልጣን መገልገል ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. የዩኒቨስቲዉ መማክርት አባላትና የተማሪዎች ክበባት ተጠሪዎችና ኃላፊዎች በአግባቡ እንዲገለግሉ የተሰጣቸዉን ኃላፊነት በህግ ከተሰጣቸዉ የስልጣን ገደብ ዉጭ አላአግባብ መጠቀም፤

ለ. የመማክርት አባላትና የክበባት ተጠሪዎችና ኃላፊዎች ሥራቸዉን ከህግና ደንብ ወይም መመሪያን መሠረት በማድረግ አለመሥራት ፤

ሐ. የተማሪዎች መማክርት አባላትና የክበባት ተጠሪዎችና ኃላፊዎች ሥልጣናቸዉን የግል ጥቅም ለማግኘት ማዋል የለባቸውም፡፡

**አንቀጽ 17፡- ለህዝብ ጥያቄ ተገቢዉን ምላሽ መስጠት**

❖ ለህዝብ ጥያቄ ተገቢዉን ምላሽ መስጠት ሥር የሚገኙትን መርሆች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ. ተማሪዎች በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ በሚኖሩት ወቅት በሀገራዊና በአከባቢያዊ በሆኑ አንገብጋቢና አስቸኳይ ሁኔታ ተፈጥሮ ከመንግስትና ከአከባቢ ማህበረሰብ በሚቀርቡ የድጋፍና የትብብር ጥያቄዎችን መተባበር እየተቻለ ሆን ተብሎ ጥያቄዎን አለመቀበልና የዜግነት ምላሽ አለመስጠት ፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>፡- የዲሲፕሊን ጥፋትና የእርምት እርምጃዎች**

**አንቀጽ 18፡- የዲስፕሊን ቅጣት ዓላማና አፈጻጸም**

**18.1.፡- በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የሚወሰድ የዲስፕሊን ቅጣት ዓላማ**

ሀ. በሰነ-ምግባር የታነፁ ተማሪዎችን ለማፍራት፡

ለ. ተማሪዎች የሥነ-ምግባር ግድፈቶችን እንዳይፈጽሙ ለማስተማርና ፈጽመዉ ሲገኙ በማረም ተገቢዉን የእርምት እርምጃ ለመዉሰድና የማይታረሙ ሆነዉ ሲገኙ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ለማድረግ፡፡

**18.2፡- በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የሚወሰድ የዲስፕሊን ቅጣት አፈጻጸም**

ሀ. ተማሪዎች ማድረግ የሚገባቸዉን ባለማድረጋቸዉ ወይም ማድረግ የማይገባቸውን በማድረጋቸው ስለጥፋታቸዉ በፍትሃብሔር ወይም በወንጀል ወይም በሁለቱም ህጎች ተጠያቂነታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ያደረሱት ጥፋት ወይም የዲስፕሊን ጉድለት በዚህ የሥነ-ምግባር መመሪያ መሠረት ተገቢዉን የቅጣት እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡፡

ለ. በዲስፕሊን ጥፋት የሚፈጸሙ ቅጣቶችን በማናቸዉም ፍርድ ቤት የሚሰጠዉን ዉሳኔ ሣይጠብቁ ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 19፡- የዲስፕሊን ቅጣት ዓይነቶች**

**19.1፡- ቀላል የዲስፕሊን ቅጣት ዓይነቶች ፤**

ሀ. በምክርና በቃል ማስጠንቀቅያ

ለ. የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ

ሐ.ማሕበራዊ አገልግሎት(ግቢ ማጽዳት፡ችግኝ መትከል፡ቤተመፃህፍት

ማገልገል፡ምግብ ቤት ማገልገልና ሌሎችም)

**19.2፡- ከባድ የዲስፐሊን ቅጣቶች**

ሀ. ለአንድ ሴሚስተር ከት/ት ገበታ የሚያሳግዱ

ለ. ለአንድ ዓመት (ሁለት ሴሚስተር) ከት/ት ገበታ የሚያሳግዱ

ሐ. ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱና

መ. ለመጨረሻ ጊዜ ከት/ት መርሀ ግብር የሚያሰናብቱ ናቸው፡፡

**19.3፡- ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች**

**ሀ. በምክር፣ በቃል ማስጠንቀቂያዎች እና በማሕበራዊ አገልግሎት የሚታለፉ የሥነ-ሥርዓት ግድፈቶች**

1. ህጋዊ ከሆኑ የዩኒቨርሲቲና የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ለሚቀርብ ጥያቄዎች ግልጽ ምላሽ ወይም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፡፡
2. የዩኒቨርሲቲዉ መማክርትና የተለያዩ ክበባት ለሚያስተላልፉት ዉሣኔ ተገቢዉን ማብራሪያ ወይም ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፡፡
3. ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸዉ ለቀሩባቸዉና ለሚቀሩባቸዉ ቀናት ህጋዊና ግልጽ መረጃ ለሚመለከተዉ አካል አለማቅረብ ፣
4. በዩኒቨርስቲው የሚወጡ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን አለማክበርና አለመከታል፡፡
5. ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸዉ በመልካም ሥነ-ምግባር ግምባር ቀደም በመሆን የሚጠበቅባቸዉን መልካም አሪአያነት አለማሳየት
6. የመመገቢያ ዕቃዎችን በተገቢዉ ቦታ ያለማስቀመጥ /ያለመመለስ/
7. በምግብ ቤት ዉስጥ እጅን መታጠብ
8. በመማሪያ ክፍሎች፣በአዳራሾችና በአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ወንበሮችና ጠረጴዛዎችን ከቦታ ቦታ ማዘዋወር
9. ዉሃና የኤሌክትሪክ ሃይል ያለአግባብ መጠቀም /ማባከን/
10. በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ያሉ አትክልቶች መርገጥ/መቁረጥ/
11. በመኝታ ቤት ግድግዳዎች፣ ህንፃዎች፣ መስኮቶች፣ በሮችና፣ወ.ዘ.ተ. ላይ ስዕል መለጠፍና ጹሑፎችን መጻፍ
12. በእጅና ፊት መታጠቢያ ቦታዎች ላይ ልብስ ማጠብ፤
13. የመኝታ ክፍል ያለፈቃድ መቀየር
14. ሌሎች መሰል የሥነ-ምግባር ችግሮችና ግድፈቶች
15. በምግብ ቤቶችና በሌሎችም የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች እንዲሁም አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ሁሉ የአገልግሎት ተራን አለመጠበቅ፤
16. ከተመደቡበት ምግብ ቤት ዉጪ በሌላ ምግብ ቤት ሲመገቡ መገኘት

17. ከመኝታ ቤትና ከሌሎች አገልግሎቶች ተጋሪዎች ጋር ተገባብቶና ተስማምቶ ለመኖር ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት፡፡

18. ባልተመደበበት መኝታ ክፍል ከሌላ ተማሪ ጋር ተደብሎ መተኛት ወይም የተባረረ ተማሪ አስተኝቶ መገኘት

19.የመኝታ ቤትንና የራስን ንጽህናን አለመጠበቅ፣ አልጋን አለማንጠፍና በአልጋዎች ላይ መጋረጃዎችን መወጠር

20. አግባብ ያላቸዉ ክፍሎች ጥሪ ሲያደርጉ አለመቅረብ፡፡

### ለ. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የሥነ-ሥርዓት ግድፈቶች

1. ከላይ የተጠቀሱትን አንዱን የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ፈጽሞ በቃል ማስተንቀቂያና በምክር የታለፈ ተማሪ ያንኑ ወይም ተመሣሣይ የሥነ-ምግባር ጉደለቶች ለሁለተኛ ጊዜ ፈጽሞ ሲገኝ፡፡

2. የዩኒቨርስቲዉን ህግ ደንብ በመጣስ ሱስ በሚያስይዝ መድሃኒት ወይም በአደንዛዥ እጽ ሱስ በመመረዝ ወይም በልማዳዊ መጠጥ ተጽዕኖ ምክንያት ትምህርትን በአግባቡ አለመከታተልና ተገቢ ያልሆኑ አድራጎት መፈጸም ፡፡

3. በግልና ማህበራዊ ህይወታቸዉ ዩኒቨርስቲዉንና የዩኒቨርስቲዉን ማህበረሰብ መልካም ግምትና አመኔታ የሚያሳጣ ድርጊት መፈጸም፡፡

4. የተሣሣተ መረጃን በተለይም ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች በመስጠት ህገ-ወጥ ተግባራትን መፈጸም፡፡

5. ህጋዊና ግልጽ ባልሆኑ መንገዶች ወደ ግቢ መግባት ወይም መዉጣት ወይም ንብረት ማዉጣት ወይም ማስገባት

6. በማንኛዉም አጋጣሚ ከዩኒቨርስቲዉ የተረከበውን ማንኛዉም ዓይነት ንብረት ወይም መገልገያ በጥንቃቄ አለመያዝና ማበላሸት፡፡

7. በዩኒቨርስቲዉ ውስጥ የሚገኙ ወይም የሚሰጡ የጋራ አገልግሎቶችን እንደ ሻዉር፣ ሽንት ቤት፣ ቤተ-መጻህፍት፣ ማደሪያ ዶርም፤ የመሳሰሉትንና ሌሎች አግልሎቶችን በግል ወይም በቡድን መጠቀም ወይም ለመጠቀም መሞከር፡፡

8. ተማሪዎች በትምህርት ቆይታቸዉ ከሙያቸዉ ጋር በተያያዘ መልኩ ወይም ከዩኒቨርስቲዉ ሥራ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚያዉቋቸዉን ሚስጢሮች አለመጠበቅና የዩኒቨርስቲዉን መልካም ስም ማጉደፍ ፡፡

9. የዩኒቨርስቲዉን መታወቂያ ካርድ ወይም የአገልግሎት መለያ ካርድ ወይም የመመገቢያ ካርድ ለሌላ ግለሰብ አሣልፎ መስጠት

10. በዩኒቨርስቲዉ ወስጥ ስልጣን ባለዉ አካል የሚወጡ ልዩ ደንቦችን ለምሳሌ እንደ ቤተ-መጻሐፍት፣ ቤተ- ሙከራ፣ ማደሪ ዶርም እና ሌሎች ደንቦችን ሆን ብሎ መጣስ

11. ህጋዊ በሆነ መልኩ ከዩኒቨርስቲ ከተባረረ በኃላ በዩኒቨርስቲዉ ውስጥ መቆየት (መኖር) እንዲሁም በህጋዊ መልኩ የተባረረዉን ተማሪ በግቢዉ ውስጥ ማስጠጋት ወይም ማኖር እና ተማሪ ያልሆነዉን ግለሰብ ማኖር፣ማሣደር ወይም ማስጠጋት

12. ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸዉ የዩኒቨርስቲዉን ስምና ክብር የሚያቃልል፣ መተማመንና መልካም አንድነት የሚያጠፋ ተግባርና እንቅስቃሰ ላይ መሰማራት

13. በተማሪዎች ማደሪ፣ በላይብረሪና በመማሪ ክፍሎች አካባቢ ሌሎችን በሚያዉክ መልኩ ድምጽን ከፍ አድርጎ መጮህ ወይም መነጋገር

14. ሥር የሰደደ የጥላቻ ባህል በዩኒቨርስቲዉ ማህበረሰብና በአካዳሚክ ስታፍ ላይ ማሣየት ወይም ማንጸባረቅ

15. በመኝታ ክፍል ዉስጥ ምግብን ማብሰል፣ ሻይና ቡና ማፍላት፣ ያልተፈቀደ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ለምሳሌ ካዉያ፣ ማሞቂያ ወ.ዘ.ተ.መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት

16. በመግቢያ በር፣ በምግብ ቤት፣ በአብያተ መጻህፍት፣ በፈተና ክፍል ወ.ዘ.ተ የመታወቂያ ካርድ ወይም የአገልግሎት መለያ ካርድ ሲጠየቅ ለማሣየት ፈቃደኛ አለመሆን

17. በመማሪያ ክፍሎች፤ በመመገቢያና በስብሰባ አዳራሾች ዉስጥ ሲጋራ ማጨስ

18. ወደ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ የመጨረሻ መግቢያ ሰዓት ተብሎ በዩኒቨርስቲዉ የተደነገገ የሰዓት ገደብን አለማክበር፡፡

19. በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ጫት ይዞ መግባት /ሲጠቀሙ መገኘት/

20. በመማሪያ ክፍሎች፤ በአብያተ መጻህፍት፣ በመኝታ ህንፃና በሌሎች የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችና ግድግዳዎች እንዲሁም ወንበሮች ጠረጴዛዎች ላይ መጻፍ /ስዕል መሳል/ወዘተ

21. አንድ ተማሪ በሌላዉ ላይ መዛት፣ መሣደብና ማስፈራራት

22. ያልተፈቀደለትን ማንኛዉንም ግለሰብ ወደ ምግብ ቤት ይዞ መግባት

23. ያለፈቃድ ደረቅ የሆኑ ምግቦችን ከምግብ ቤት ዉጪ ማዉጣት

24. አግባብ ያላቸዉ የዩኒቨርስቲ አካላት ወይም ኃላፊዎች የሚያወጧቸዉን መመሪያዎችና የሥነ-ሥርዓት ደንብ አለማክበር

25. የግልና የጋር ጤንነትን ሊጎዱ የሚችሉ ድርጊቶች መፈጸም (ክፍል ዉስጥ ማጨስ፤ አልኮል መጠጣት፤ጫት መቃምና ወዘተ )

26. ግቢ ዉስጥ ባልተገባ ቦታ መጸዳዳት

27. ከላይ በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱትን ጥፋት ሲፈጽሙ እያዩ ለሚመለከተዉ ክፍል አለማሳወቅ

28. በዩኒቨርስቲዉ ዉስጥ የፈተና፣ የስብሰባ፣ የምዝገባና የምረቃ ወ.ዘ.ተ. ጊዜን ማወክ

29. ሌሎች መሰል የሥነ-ምግባር ጉድለቶች መፈጸም፡፡

**19.4፡- ከባድ የዲስፕሊን ቅጣቶች**

***ሀ. ለአንድ ሴሚስቴር ከዩኒቨርስቲ የሚያሰግዱ ቅጣቶች***

1. ከላይ ከተጠቀሱት አንደኛዉን የሥነ-ምግባር ጉድለቶች ፈጽሞ በጹሑፍ ማስጠንቀቂያ የታለፈ ተማሪ ማንኛዉም ወይም ተመሳሳይ ሥነ-ምግባር ፈጽሞ ሲገኝ

2. የሀገሪቱንና የዩኒቨርስቲዉን ህግና ደንብ አለማክበር

3. በዩኒቨርስቲ ውስጥ በተማሪዎች ወይም በሌላ አካል የሚደረግ ህገ-ወጥ እንቅስቃሴን እያወቁ በጊዜ አለማጋለጥ ወይም ተባባሪ መሆን

4. ፈተናን መኮረጅ፣ ማስኮረጅ፣ ከደብተር ወይም ከወረቀት መገልበጥ ወይም መሥራት ወይም የፈተና ወረቀትን ደልዞ ወይም ጨምሮ ከመምህራን ዉጤት ለማስቀየር መሞከር

5. በዩኒቨርስቲ ዉስጥ ለሚደረጉ ነገሮች በሀሰት መመስከር

6. ዩኒቨርስቲውን ክሊኒክ መድሃኒቶችን ለሌላ ተግባር ማዋል

7. ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ቆይታቸዉ ኢ-ዲሞክራሲያዊ የሆነ እና በኃይልና በጉልበት ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን ከዩኒቨርስቲዉ ማህበረሰብ ጋር መመስረት

8. ለግጭት የሚገፋፋና አሰነዋሪ የሆኑ ነገሮችን በቃል ወይም በጹሑፍ በመማሪያ፣ በመኖሪያ፤ በመጸዳጃና በቢሮዎች ግድግዳዎች፣መዝጊያዎች መስኮቶችና ቁም ሳጥኖች ላይ መጻፍ፣ ወዘተ

9. የዩኒቨርስቲ ሠራተኞችንና መምህራን መልካም ስም በሀሰት በጹሁፍ ወይም በሌላ መንገድ ሊያጎድፍ የሚችል ድርጊቶችን መፈጸም

10.ሴት ተማሪዎችን በንግግር፣ በጽሁፍ በኃይል ወዘተ ማስፈራራት፣ መዝለፍ፣ ማስቸገር፣ ማስጨነቅና ወሲባዊ ተንኮሳ ማካሄድ

11. የተማሪዎች ሥነ-አእምሮ ሊጎዱ የሚችሉትን ኃይለ ቃሎችን በመጠቀም ( ለምሳሌ ሴት ተማሪዎችን፤ የአካል ጉዳትን፣ የሰዉነት አቋምን፣ ከባህል ጋር ግንኙነት ያላቸዉን ነገሮችን ወዘተ) ምክንያት በማድረግ ተማሪዉን የዝቅተኝነት ስሜት እንዲሰማዉ ማድረግ

12. የዩኒቨርስቲዉን ንጽህናና ጽዳት የሚጎዱ ድርጊቶችን ለማሳሌ አበቦችን መንቀል አጥር ማፍረስ፣ በዶርምና በመማሪያ ክፍሎች አከባቢ ሽንት መሽናት ወይም መጸዳዳት

13. የተለጠፉ ህጋዊ ማስታዋቂዎችን ማንሣት፣ መቅደድ፣ መደለዝ ወይም ማበላሸት

14. በአጥር ዘሎ መግባት ወይም መዉጣት

15. በስካር መንፈስ በግቢ ዉስጥ በማንኛዉም ቦታ ረብሸን መፍጠርና መጥፎ ሥነ-ምግባር ማሣየት

16. የአልኮል መጠጦችን በግቢ ዉስጥ አስቀምጦ መገኘት ወይም ሲጠቀሙ መገኘት

## ለ. ለአንድ ዓመት ከዩኒቨርስቲ የሚያሰግዱ ቅጣቶች

1. ከላይ የተጠቀሱትን የሥነ-ምግባር ግድፈትን ወይም በጽሑፍና አንድ ሴሚስቴር ቅጣት የታለፉ ተማሪዎች ማንኛዉም ወይም ተመሳሳይ የሥነ-ምግባር ጉድለት ፈፅመው ሲገኝ

2. የዩኒቨርስቲዉን ክብርና ዝና የሚጎዱ፣ የተማሪዉንና የዩኒቨርስቲዉን ማህበረሰብ የሚያዉክ ባህሪይና ተግባሪ መፈጸም ወይም ማሣየት

3. የዩኒቨርስቲዉን ማህበረሰብ ንብረት መስረቅ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ

4. ህጋዊ ያልሆኑ ጹሁፎችን በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ዉስጥ መበተን ወይም ማሰራጨት

5. ማንኛዉም ተማሪ ማሟላት የሚገባዉን ነገር አልተደረገልኝም ብሎ ሲያስብ በግል ወይም በተወካይ አማካይነት በህጋዊ መንገድ ማቅረብና ምላሽ ማግኘት ሲገባዉ ራሱንም ሆነ ሌሎችን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለአመጽ ማነሳሳት

6. በመደራጀትና ረብሻን በማነሳሳት የት/ት ክፍለ ጊዜዎች እንዳይካሄዱ ማድረግና የዩኒቨርስቲዉን የሥራ እንቅስቃሴን ማስተጓጎል

7. በፈተና ወቅት ከወረቀት መስራትና ይህንን ሊያስቆሙ፣ ከሚንቀሳቀሱ ፈታኝ መምህራን ወይም ግለሰብ ጋር ግብግብ መፍጠር ወይም ለመደባደብ መሞከር

8. ከዩኒቨርስቲዉ መምህራንና ሠራተኞች ጋር እንዲሁም እርስ በርስ ጥል ፈጥሮ መደባደብ፣ መሳደብና ማንጎጠጥ

9. በዩኒቨርስቲዉ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ድምጽ ያለዉ ወይም የሌለዉ የጦር መሣሪያ ይዞ መገኘትና ጉዳት ለማድረስ መሞከር

10. የዩኒቨርስቲ የጋር መገልገያ ቁሳቁሶችንና የሻዉር ዕዋዎችን መስበርና ማበላሸት እንዲሁም የመጻህፍት ሰነዶችን መቅደድ

11. በተቃራኒ ፆታ ህንፃ ዉስጥ መገኘት ወይም ሁኔታዎችን አመቻችቶ ተቃራኒ ፆታን ወደ መኝታ ህንፃ ለማስገባት መሞከር፡፡

12. የዩኒቨርስቲዉን ፀጥታና ሰላም ለማደፍረስ መሞከርና ማደፈረስ

13. ያአግባብ የመምህራንን ወይም የሌሎችን ሠራተኞች ወይም የዩኒቨርስቲዉን የማናጀመንት አባላት ከዩኒቨርስቲዉ ሥራቸዉ ጋር በተያያዘ ሥም ማጥፋት

14. የሌላ ሰዉ የምርምር ጹሑፍ ወይም ሥራ በሙሉም ሆነ በከፊል በመገልበጥ እንደራሱ ሥራ አድርጎ ማቅረብ ወይም ለማቅረብ መሞከር

### ሐ. ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ከት/ት ገበታ የሚያሰግዱ ቅጣቶች

1. የተለያዩ የማጭበርበር ወንጀሎችን መፈጸም ወይም ለመፈጸም ሙከራ ማድረግ ለምሳሌ አስመስሎ መፈረም፣ ህጋዊ የሆኑ ሰነዶችን መሠረዝ፣ መደለዝና አስመስሎ መሥራት
2. በዩኒቨርስቲ ግቢ ዉስጥ በዘር፣ በብሔር ፣ በፖለቲካ ልዩነት በሀይማኖት፣ በቀለም ክፍፍል ወ.ዘ.ተ. ፈጥሮ መሳደብ፣መደባደብ ፣ግጭቶችን መፍጠር
3. በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ለሌላ ሰዉ ሲፈተኑ መገኘት
4. በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ዉስጥ የግብረ -ስጋ ግንኙነት መፈጸም
5. በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ዉስጥ አደንዛዥ እጽ ወይም ድራግ መጠቀምና ይዞ መገኘት
6. በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ያልተፈቀደ ስብሰባ ማካሄድ፣ አድማ ማሳደም፣ ለማሳደም መሞከርና ህገ-ወጥ ሳላማዉ ሰልፍ ማድረግ ወይም ለማድረግ መሞከር
7. በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን መርሆች አለማክበር ወይም መጣስ

### መ. ለመጨረሻ ጊዜ ከዩኒቨርስቲ የሚያሰባርሩ ቅጣቶች

1. በዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ዉስጥ ሴት ተማሪን አስገድዶ መድፈር ወይም ለመድፈር ሙከራ ማድረግ ፡፡
2. ለሁለት ተከታታይ የት/ት ዓመታት የሚያሳግዱ ከባድ ጥፋቶችን ፈጽሞ በተወሰደዉ እርምጃ መሻሻል ሳያሳይ ለሁለተኛ ጊዚ ማንኛዉንም ተጨማሪ ጥፋት መፈጸም
3. ድምጽ ባለዉ ወይም በሌለዉ መሣሪያ የዩኒቨርስቲ አባል የሆነ ግለሰብን መጉዳት ወይም ለመጉዳት ሙከራ ማድረግ
4. ሆን ብሎ የዩኒቨርስቲዉን ንብረት ለማጥፋት መሞከር ወይም ማጥፋት
5. ማንኛዉንም የስርቆት ተግባር መፈጸም ወይም በድርጊቱ መተባበር
6. የአንድን ግለሰብ ብሔር ወይም ሀይማኖት በማንቋሸሽ ፀያፍ ቃል መሠንዘር ወይም በተለያዩ ቦታ ጽፎ መገኘት

### አንቀጽ 20 ፡- ተመራቂ ተማሪዎች የዲስፒሊን ግድፈትን ፈጽመዉ ሲገኙ የሚወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች

*ተመራቂ ተማሪዎች ማለት፡- የመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች ሲሆኑ የመጨረሻዉን መንፈቅ ዓመት ትምህርት ተፈትነዉ ለመመረቅ የተዘጋጁ እጩ ምሩቃን ጥፋት ሲፈጽሙ የጥፋቱን ሁኔታ በመመልከት በሚከተለዉ መልኩ የሥነ-ምግባ እርምጃ መዉሰድ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁም መሰረት ከላይ በአንቀጽ 19 (አሥራ ዘጠኝ) ስር የተደነገጉ ቅጣቶች እንዳሉ ሆነው፡-*

20.1 በቃል ማስጠንቀቂያ የሚታለፉ ተብለዉ የተጠቀሱትን በቃል ማስጠንቀቂያ

20.2 በጹሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚታለፉ ተብለዉ የተጠቀሱትን በጹሁፍ ማስጠንቀቂያ

20.3 ለአንድ ሲሚስቴር የሚያስቀጡ ጥፋቶች ፈጽሞ ሲገኝ ለአንድ ሴሚስቴር ከመመረቅ እንዲዘገይ ይደረጋል፡፡

20.4 ለአንድ የትምህርት ዓመት ከትምህርት ገበታ የሚያሳግዱ ከባድ ጥፋቶች፣ እንዲሁም ለሁለት የትምህርት ዓመት ከትምህርት ገበታ የሚያሳግድ ከባድ ጥፋቶች የተባሉትን የፈጸመ ተመራቂ ተማሪ ለሁለት ተከታታይ ሴሚስተር /አንድ ዓመት /ማንኛዉንም የትምህርት ማስረጃ ይያዝበታል፡፡የድጋፍ ደብዳቤም ይከለከላል፡፡

20.5 ተመራቂ ተማሪ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ከዩኒቨርስቲ ሙሉ በሙሉ ሊያሳግድ የሚችሉ የስነ-ምግባር ግድፈት የፈጸመ ተመራቂ ተማሪ ለሁለት ዓመታት ማንኛዉንም ዓይነት የትምህርት ማስረጃ ይያዝበታል፡፡ የድጋፍ ደብዳቤም ይከለከላል ወይም ይታገድበታል፡፡

20.6 በዚህ መመሪያ ዉስጥ ከተጠቀሱት ዉጪ ተማሪዎች አንዳንድ ከፍተኛ ጥፋቶችን ቢፈጽሙ ዩኒቨርስቲዉ በተማሪዎች ደህንነትና ጥበቃ ክፍል፣ በተማሪዎች ዲስፕሊን ኮሚቴ፣ በፋካልቲ ዲኖችና በተጨማሪ አግባብ ባላቸዉ መደበኛ የህግ ክፍሎች እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

20.7 በአካዳሚክ ዉጤት ማነስ ምክንያት፣ በዲሲፕሊን ግድፈት ምክንያት ከዩኒቨርስቲዉ እንዲታገዱ የተደረጉ ተማሪዎች ያለበቂ ምክንያት በግቢዉ ዉስጥ ሲንቀሳቀሱ ቢገኙ የመልሶ ቅበላ (Readmission) ጥያቄያቸዉ ይሰረዛል፡፡አግባብ ባለዉ የህግ አካል ቀርበዉ ዉሣኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

**አንቀጽ 21፡- የዲስፒሊን ክስ አመሰራረትና እርምጃ አወሳሰድ**

1. ክስ ማንኛውም የዩኒቨርስቲ ማህበረሰብም ሆነ ተማሪ ለትምህርትም ሆነ ለማህበራዊ አገልግሎት ከሄዱባቸው ተቋማት፣ ግለሰቦችና የአከባቢው ማህበረሰብ ከበቂ ማስረጃ ጋር ለዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. የዩኒቨርስቲው ፕሬዝዳንትም የቀረበውን ክስ ለዲሲፕሊን ኮሚቴው በጽሑፍ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
3. የዲሲፒሊን ኮሚቴ ተከሳሽ ተማሪ ክሱ በጽሁፍ እንዲደርሰውና ቀርቦም እንዲከላከል ወይም እንዲከራከርና ማስረጃ (የጽሁፍ፣የቃል ወይም የሰው ምስክር) እንዲያቀርብ ማድረግ አለበት፡፡
4. የዲስፕሊን ኮሚቴ ከከሣሽም ሆነ ከተከሣሽ የሚቀርቡ ማስረጃዎችንና ምስክሮችን በመሰብሰብና በማጣራት ላይ የተመረኮዘ ዉሣኔ መስጠት ወይም የውሳኔ ሀሳብ ለፕሬዝዳንቱ ማቅረብ አለበት፡፡
5. የዲሲፒሊን ኮሚቴ የመጨረሻ የክሱን ውሳኔ ለተከሳሽ ተማሪ በጽሁፍ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡
6. በጥፋተኝነት የተወሰደዉን ማንኛዉም እርምጃ ተከሣሽ በዉሣኔዉ ላይ ቅሬታ ካለዉ በአንድ ሣምንት ጊዜ ዉስጥ ለዩኒቨርስቲዉ ፕሬዚዳንት ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታዉም ከፕሬዝዳንቱ በአንድ ሳምንት ዉስጥ ምላሽ ካላገኘ በኮሚቴው የተሰጠው ዉሣኔ የፀና ይሆናል፡፡

**<u>ክፍል አራት</u>፡- መረጃ በመስጠት መተባበር**

**አንቀጽ 22፡- በጥቆማ ስለማሳወቅ**

1. ማንኛዉም ተማሪ በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተካተቱትን መርሆዎችን የሚጻረር የሥነ-ምግባር ጉድለት መፈጸሙን በማንኛዉም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን ለሚመለከተዉ ክፍል ማሣወቅ አለበት
2. የሚያቀርበዉ ጥቆማ እዉነተኛ፣ ያልተዛባ፣ ከበቀል የፀዳ፣ አሣሣች ያልሆነ ምክንያታዊ በሆነ እምነት ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. ጥቆማ አቅራቢዉ ከማንኛዉም የበቀል ጥቃት የመጠበቅ መብት አለዉ፡፡
4. ጥቆማ አቅራቢዉ ማንነቱ እንዳይገለጽ ከፈለገ ማንነቱ በሚስጢር መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 23 ፡-የመተባበር ግደታ**

ማንኛዉም ተማሪ ለዲስፕሊን ሥራ የሚያስፈልገዉንና የሚጠየቀዉን መረጃ በመስጠት የመተባበር ግደታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 24፡- መመሪያዉን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት በማናቸዉም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል ፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የሠራተኛ ሥነ-ምግባር ድንጋጌዎች</u>

**<u>ክፍል አንድ</u>፡ -የዲስፐሊ አፈጻጸም**

በፌደራል የመንግስት ሠራተኞች የዲስፐሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ቁጥር 77/1994 መሠረት የዲስፒሊን ክስ አመሰራረትና እርምጃ አወሳሰድ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

**1.የዲስፐሊን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣንና ኃፊነት**

**1.2 ቀላል የዲስፐሊን ጥፋቶች**

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኞች ቀላል የዲስፐሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ እንደ ጥፋቱ ክብደት ፡-

፩. የቅርብ ኃፊው የቃል ማስጠንቀቂያ የመስጠት

፪. ከዋና ክፍል ያላነሰ ደረጃ ያለው የሚመለከተው ኃላፊ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት  ወይም

፫. የመሥሪያ ቤቱ የአስተዳደር ኃላፊ እስከ አንድ ወር ደመወዝ የመቅጣት ሥልጣንና ኃፊነት ይኖረዋል፡፡

**1.3 ከባድ የዲስፐሊን ጥፋቶች**

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኞች ከባድ የዲስፐሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በዚህ ደንብ መሠረት ተጣርቶ ሲቀርብለት እንደ ጥፋቱ ክብደት እስከ ሦስት ወር ደመወዝ የመቅጣት ወይም ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ የማድረግ ወይም ከሥራ የማሰናበት  ሥልጣንና ኃፊነት ይኖረዋል፡፡

**1.4 ከሥራ ስለማገድ**

በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 በአንቀጽ ፷፪ በተቀመጠው መሠረት ተፈጻም ይሆናል፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>፡- የዲስፐሊን ምርመራ**

**2.1 የተፋጠነ የዲስፐሊን ምርመራ**

፩. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፩ ወይም ፪ መሠረት የሚያስቀጣ ቀላል የዲስፐሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነና የሚመለከተው ኃላፊ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ጥፋቱን የሚያጣሩ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የመንግስት ሠራተኞች ሊመድብ ይችላል፡፡

፪. የተመደበው አጣሪ የመንግስት ሠራተኛው ለቀረበበት ክስ በጽሑፍ መልስ እንዲሰጥ የክሱን ጽሑፍ ይልክለታል፡፡

፫. የመንግስት ሠራተኛው ጥፋቱን አምኖ መልስ የሰጠ እንደሆነ አጣሪው  በዚሁ ላይ ተመሥርቶ የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል፡፡

፬. የመንግስት ሠራተኛው የቀረበበትን ክስ በመካድ መልስ የሰጠ እንደሆነ አጣሪው አግባብ ያላቸውን ማስረጃዎች ከመረመረ በኃላ ለሚመለከተው ኃላፊ የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል፡፡

፭. የሚመለከተው ኃላፊ የቀረበለትን የውሣኔ ሃሣብ መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል ሆኖም የሚወሰነው የዲስፐሊን ቅጣት ከራሱ ሥልን በላይከሆነ የበኩሉን አስተያየት ጨምሮ ለሚመለከተው ኃላፊ ያቀርባል  ፡፡

**2.2 መደበኛ ምርመራ**

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፫ ወይም አንቀጽ ፬ መሠረት የሚያስቀጣ  የዲስፐሊን ጥፋት የተከሰሰ እንደሆነ ክሱ የሚከተሉት ድንጋጌዎች ተከትሎ ይጣራል፡፡

## 2.3 የክስ ጽሑፍ

፩. የዲስፕሊን ክስ ጽሑፍ የመንግስት መሥሪያ ቤቱ የአስተዳደር ኃላፊ የፈረመበትና የመሥሪያ ቤቱ ማኅተም የተደረገበት ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

ሀ) የተከሣሹን ስም፤

ለ) የጥፋቱን ዝርዝር፤

ሐ) ጥፋቱ የተፈጸመበት ጊዜ እና ቦታ፤

መ) የተጣሰው የሕግ ድንጋጌ እና

ሠ) የማስረጃዎች ዝርዝር፤

፪. ሠራተኛው ከአንድ በላይ በሆነ ጥፋት የተከሰሰ ከሆነ እያንዳንዱ ጥፋት ተለይቶ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ (ለ)-(ሠ) በተመለተው መሠረት መገለጽ አለበት፡፡

## 2.4. ክስን ስለማሻሻል

1. በዲስፐሊን ክስ ጽሁፍ ውስጥ የተገለጸውን የጥፋት ዝርዝር በሚመለከት መሠረታዊ በሆኑ ነጥቦች ላይ ስህተትበወይም ግድፈት መኖሩ ሲታወቅ የውሳኔ ሀሣብ ከመቅረቡ በፊት በማናቸውም ጊዜ ክሱን ማሻሻል ይቻላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሠረት የመንግስት መሥሪያ ቤቱ አስተዳደር የዲፕሊን ክስን ሊያሻሽል የሚችለው በራሱ አነሣሽት ወይም ክሱን በሚያጣራው የዲስፐሊን ኮሚቴ ጥያቄ መሠረት ነው፡፡

## 2.5. ክስ የሚቋረጥበት ሁኔታ

1. የዲስፐሊ ክስ የቀረበበት የመንግስት ሠራተኛ በማናቸውም ምክንያት አገልግሎት የተቋረጠ እንደሆነ የክሱ መታየት ይቆማል፡፡
2. በከባድ የዲስፐሊን ጥፋት የተከሰሰ የመንግስት ሠራተኛ በራሱ ፍቃድ ሥራውን በመልቀቁ አገልግሎቱን አቋርጦ በሌላ በማናቸውም የመንግስት መሥሪያ ቤት ተመልሶ የተቀጠረ እንደሆነ የቋረጠው ክስ መታየቱ ይቀጥላል፡፡

## 2.6. ክስን ስለማሣወቅ

1. የዲስፐሊን ኮሚቴ ክስ የቀረበበት ሠራተኛ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ የክሱን ጽሑፍና ማስረጃዎች ቅጅ አያይዞ የክስ ማስታወቂያ ይልክለታል፡፡
2. የክስ ማስታወቂያው ክሱ የሚሰማበትን ቦታ፤ቀንና ሰዓት የሚገልጽ ሆኖ ክሱ ከሚሰማበት ቀን ቢያንስ ከ ፲ ቀናት በፊት ለተከሣሹ መድረስ አለበት፡፡
3. ሠራተኛው ሊገኝ ባለመቻሉ ወይም ለመቀበል ፈቃዳኛ ባለመሆኑ የክስ ማስታወቂያውን ለመስጠት ያልተቻለ እንደሆን በመሥሪያ ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ተለጥፎ ለ፲፫ ቀናት እንዲቆይ ይደረጋል፡፡

## 2.7. የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ መሠረት የክስ ጽሑፍ የደረሰው ተከሣሽ፡-

ሀ. ክሱ በአዋጁ መሠረት በይርጋ የተጋደ ከሆነ ወይም

ለ. ተፈፀመ የተባለው ድርጊት በዲስፐሊን ሊያስከስስ የማይችል ወይም

ሐ. በተከሰሰበት ጉዳይ ላይ ቀደም ሲል ውሣኔ የተሰጠበት ከሆነ ክሱ ሊታይ አይገባውም በማለት መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. የዲስፐሊን ኮሚቴው፡-

ሀ. መቃወሚያውን የተቀበለው እንደሆነ ክሱ እንዲዘጋ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል፤ ወይም

ለ. መቃወሚያውን ያልተቀበለው ከሆነ ተከሣሹ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ያዘዋል፡፡

**2.8. የክስ መልስ**

1. የዲስፐሊን ክስ የቀረበበት የመንግስት ሠራተኛ ክሱን የሚያምን ወይም የሚክድ ከሆነ ይህንኑ በዝርዝር በመግለጽ መልሱን በጽሑፍ ያቀርባል፡፡
2. የክስ መልስ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ የፈረመበት ሆኖ

   ሀ. በክሱ ስለተገለፀው እያንዳንዱ ዲርጊት ወይም ጥፋት የተሰጠውን መልስ እና

   ለ. ለተከሣሹ እንዲታዩለት የሚፈልጋቸውን የመከላከያ ማስረጃዎች ዝርዝር መያዝ አለበት

3. ተከሣሽ ከዘረዘራቸው የመከላከያ ማስረጃዎች መካከል በእጁ የሚገኙትን የጽሁፍ ማስረጃዎች ቅጂ አያይዞ ማቅረብና የዲስፐሊን ኮሚቴው እንዲያስቀርብለት የሚጠይቃቸውን ማስረጃዎች ደግሞ በማን እጅ እንደሚገኙ መግለጽ አለበት፡፡

**2.9. በማመን ወይም በመካድ ስለተሰጠ መልስ**

1. ተከሣሹ ክሱን በማመን መልስ የሰጠ እንደሆነ የዲስፐሊን ኮሚቴው ተጨማሪ ማጣራት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው በስተቀር የቀረበውን ክስና የተሰጠውን መልስ በመመርመር የውሣኔ ሃሣብ ያቀርባል፡፡
2. ተከሣሽ የጥፋቱን ድርጊት በመካድ መልስ የሰጠ እንደሆነ የዲስፐሊን ኮሚቴው የከሣሹንና የተከሣሹን ምስክሮች በመስማትና የጽሑፍ ማስረጃዎቻቸውን በመመርመር ክሱን ያጣራል፡፡

**<u>ክፍል ሦስት</u>፡- መብቶችና ግዴታዎች**

በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 መሠረት የሠራተኛ መብት ፤ግዴታዎች እና የዲስፒሊን እርምጃ አወሳሰድ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

**3.1. የደመወዝ ክፍያ**

1/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በየወሩ መጨረሻ ለሠራተኞቹ ወይም ለሕጋዊ ወኪሎቻቸው የደመወዝ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

2/ የማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዝ፣

ሀ) ሠራተኛው ስምምነቱን በጽሑፍ ሲገልጽ፣

ለ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣

ሐ) በሕግ በተደነገገው መሠረት፣ ካልሆነ በስተቀር ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ አይችልም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ወይም (ሐ) መሠረት ከሠራተኛ ደመወዝ በየወሩ የሚቆረጠው ከደመወዙ አንድ ሦስተኛ አይበልጥም፡፡

### 3.2. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት

በዚህ አዋጅ በሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከቱት ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1/ የመንግስት ሠራተኞች በመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የማድረግ፤

2/ የመሥሪያ ቤቱ የሥራ አካባቢ ከማንኛውም ዓይነት ኃይማኖታዊ ተግባራት ነጻ መሆኑን የማረጋገጥ፤

3/ ለእያንዳንዱ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ ዝርዝር መግለጫ የመስጠትና በሥራ ዕቅድ ላይ ተመሥርቶ የሠራተኛውን የሥራ አፈጻጸም ውጤት የመለካት፤

4/ ለመንግሥት ሠራተኞች ለሥራ የሚያስፈልጓቸውን መሣያዎች የማቅረብና አጠቃቀማቸውን የማሳወቅ፤

5/ የሥራ አካባቢውን ለመንግሥት ሠራተኞች ጤንነትና ደህንነት አመቺ የማድረግ፡፡

### 3.4. የመንግሥት ሠራተኞች ግዴታዎች

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፤

1/ ለሕዝብና ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ መሆንና የሕግ የበላይነትን የማክበር፤

2/ መንግሥት የሚያወጣቸውን ሕጎችና ፖሊሲዎችን በብቃት የመፈጸም፤

3/ በማናቸውም ሁኔታ ሕዝብንና ሀገርን ያለአድልዎ የማገልገል፤

4/ መላ ዕውቀቱንና ችሎታውን ለሕዝብ አገልግሎት የማዋል፤

5/ በሥራ ዝርዝሩ የተመለከቱትንና በቅርብ ኃላፊው የሚሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ የመፈጸም፤

6/ በማናቸውም ሁኔታ በሥራ ቦታ ላይ የግል እምንነቱን ወይም ኃይማኖቱን የሚያንጸባርቅ ተግባር አለመፈጸም፤

7/ ሚስጢር ተብለው የተለዩና በሥራው አጋጣሚ ያወቃቸውን የመሥሪያ ቤቱን ምስጢሮች የመጠበቅ፤

8/ በተገልጋዮች መካከል በፆታ፣ በቋንቋ፣ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌሎች ልዩነት በሚፈጥሩ ሁኔታዎች መድሎ ያለመፈጸም፤

9/ ለመስሪያ ቤቱ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚያጓድል ወይም በማናቸውም አኳኋን ከተመደበበት ሥራ ጋር የሚቃረን ወይም ከመንግስት ሠራተኝነቱ ጋር የማይጣጣም ማናቸውንም ሌላ ሥራ ያለመስራት፤

10/ ሥራውን ለፖለቲካ ጥቅሙ ያለማዋልና በዚህም ምክንያት አድሎ ያለመፈጸም፤

11/ በመንግስት ሠራተኝነቱ ለሰጠው ወይም እንዲሰጥ ለሚጠበቀው አገልግሎት ማንኛውንም ዓይነት ስጦታ ወይም ዋጋ ያላቸው ነገሮች ያለመጠየቅ ወይም ያለመቀበል፤

12/ ለሥራ ማከናወኛ የተሰጡትን መሣሪያዎችና መገልገያዎች በአግባቡ የመጠቀምና የመጠበቅ፤

13/ ከኤች አይ ቪ/ኤድስ በስተቀር ከሥራው ጋራ በተያያዘ በበቂ ምክንያት የህክምና ምርመራ እንዲያደርግ በመንግስት መሥሪያ ቤቱ ሲጠየቅ ለምርመራ የመቅረብ፤

14/ ስለሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ጥበቃ የወጡ መመሪያዎችን የማክበር፡፡

**3.5 በዕዳ የመጠየቅ ኃላፊነት**

ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ለሥራው ማከናወኛ በተሰጡት መሣሪያዎችና መገልገያዎች ላይ በሚደርስ ጉዳት ወይም ጥፋት በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ጉዳቱ ወይም ጥፋቱ በሠራተኛው ቸልተኝነት ወይም ሆነ ተብሎ በተፈፀመ ድርጊት ምክንያት የደረሰ እንደሆነ ነው፡፡

**<u>ክፍል አራት</u>፡- የዲስፐሊን እርምጃዎች እና የቅሬታ አፈታት**

**4.1. የዲስፐሊን ቅጣት ዓላማ**

የዲስፐሊን ቅጣት ዓላማ የመንግሥት ሠራተኛው በፈጸመው የዲስፐሊን ጉድለት ተፀፅቶ በአመለካከቱና በሥነ-ምግባሩ እንዲታረምና ብቁ ሠራተኛ እንዲሆን ለማስቻል ወይም የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ለማሰናበት ነው፡፡

**4.2 .የዲስፐሊን ቅጣት ዓይነቶችና አመዳደብ**

1/ የዲስፐሊን ጉድለት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት ቅጣቶች አንዱ ሊወሰንበት ይችላል፤

ሀ) የቃል ማስጠንቀቂያ፤

ለ) የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፤

ሐ) እስከ አሥራ አምስት ቀን ደመወዝ የሚደርስ መቀጮ፤

መ) እስከ ሦስት ወር ደመወዝ የሚደርስ መቀጮ፤

ሠ) እስከ ሁለት ዓመት ለሚደርስ ጊዜ በሥራ ደረጃ እና ደመወዝ ዝቅ ማድረግ፤

ረ) ከሥራ ማሰናበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) እስከ (ሐ) የተዘረዘሩት ቅጣቶች ቀላል የዲሲፐሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(መ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩት ቅጣቶች ከባድ የዲሲፐሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሠ) መሠረት ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ በማድረግ የተቀጣ የመንግሥት ሠራተኛ የቅጣት ጊዜውን ሲያጠናቅቅ፣

ሀ) ከመቀጣቱ በፊት ይዞት ከነበረው የሥራ መደብ ጋር ተመሳሳይ ክፍት የሥራ መደብ ካለ ያለምንም ተጨማሪ የደረጃ ዕድገት ሥነ-ሥርዓት፣

ለ) ከመቀጣቱ በፊት ይዞት ከነበረው የሥራ መደብ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ክፍት የሥራ መደብ ካልተገኘ ክፍት የሥራ መደቡ በተገኘ ጊዜ ያለምንም ተጨማሪ የደረጃ ዕድገት ሥነ-ሥርዓት፣ በሥራ መደቡ ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

5/ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በዲስፐሊን ከተቀጣ በኋላ ቅጣቱ በሪከርድነት ሊቆይና ሊጠቀስበት የሚችለው፣

ሀ) ቀላል የዲስፐሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት፣

ለ) ከባድ የዲስፐሊን ቅጣት ከሆነ ቅጣቱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ለአምስት ዓመት ይሆናል፡፡

## 4.3. ከባድ የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች

የሚከተሉት ጥፋቶች ከባድ የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች ናቸው፤

1/ ሕጋዊ ትእዛዝን ባለማክበር፣ በቸልተኝነት፣ በመለገም፣ ወይም ሆነ ብሎ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ወይም የመንግስትን ፖሊሲ ባለመከተል በሥራ ላይ በደል ማድረስ፤

2/ ጉዳዮችን ሆን ብሎ ማዘግየት ወይም ባለጉዳዮችን ማጉላላት፤

3/ ሥራ እንዳይሠራ ሆን ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር፤

4/ በቀላል የዲስፐሊን ቅጣት እርምጃዎች ባለመታረም ያለበቂ ምክንያት በተደጋጋሚ ከሥራ መቅረት ወይም የሥራ ሰዓት አለማክበር፤

5/ በሥራ ቦታ በጠብ አጫሪነት መደባደብ፤

6/ በልማዳዊ ስካር ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሱስ በመመረዝ ሥራን መበደል፤

7/ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፤

8/ በሥራ ቦታ ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም፤

9/ የሌብነት ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት መፈጸም፤

10/ የማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም፤

11/ በመሥሪያ ቤቱ ንብረት ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፤

12/ በሥልጣን አለአግባብ መጠቀም፤

13/ በሥራ ቦታ ላይ ፆታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት መፈፀም፤

14/ በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያለው ሌላ የዲሲፐሊን ጉድለት መፈጸም፡፡

## 4.4. የዲስፐሊን እርምጃ አወሳሰድ

1/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት መደበኛ የዲስፐሊን ምርመራ የሚያካሂድና የውሳኔ ሀሳብ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ የዲስፐሊን ኮሚቴ ማቋቋም አለበት፡፡

2/ የዲስፐሊን ቅጣት የማንኛውንም ፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይጠብቅ ወይም ሳይከተል ሊወሰን ይችላል፡፡

## 4.5. ሠራተኛን ከሥራ አግዶ ስለማቆየት

1/ ማንኛውንም የመንግሥት ሠራተኛ ከሥራ አግዶ ማቆየት የሚቻለው፣

ሀ) ከተጠረጠረበት ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማበላሸት፣ በመደበቅ ወይም በማጥፋት ምርመራውን ያሰናክላል፣

ለ) በመንግሥት ንብረት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ያደርሳል፣

ሐ) ከተከሰሰበት ጥፋት ክብደት አንጻር የሌሎችን ሠራተኞች ሞራል የሚነካ ወይም የተገልጋዩ ሕዝብ በመሥሪያ ቤቱ ላይ ሊኖረው የሚገባውን እምነት ያዛባል፣ወይም

መ) ተፈጸመ የሚባለው ጥፋት ከሥራ ያስወጣል፣ ተብሎ ሲገመት ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አንድ ሠራተኛ ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ ሊቆይ የሚችለው ከሁለት ወር ለማይበልጥ ጊዜ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከሥራና ከደመወዝ ታግዶ እንዲቆይ የሚደረግ የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ ሥራው ታግዶ የሚቆይበት ጊዜና ከሥራ የታገደበት ምክንያት በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም በተወካዩ በጽሑፍ እንዲገለጽለትና ሚኒስቴሩም በግልባጭ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

4/ የመንግሥት ሠራተኛው በተከሰሰበት የዲስፐሊን ጥፋት ምክንያት ከሥራ እንዲሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር በእግዱ ወቅት ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ያለወለድ ይከፈለዋል፡፡

5/ የመንግሥት ሠራተኛው ከሥራ በመታገዱ ምክንያት ከዕግዱ ጋር ያልተያያዙ ሌሎች መብቶቹንና ግዴታዎቹን ተፈጻሚነት አያስቀርም፡፡

6/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም ከሥራና ደመወዝ ታግዶ የቆየ ሠራተኛ ከሥራ እንዲሰናበት ወይም በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ደመወዙ እንዲከፈለውና ወደ ሥራው እንዲመለስ ሳይደረግ የዕግዱ ጊዜ ካበቃ፣

ሀ) የመዘግየቱ ምክንያት የዲስፐሊን ክሱን የማጣራቱ ሂደት ውስብስብነት ከሆነ የመንግሥት ሠራተኛው ግማሽ ደመወዙ እየተከፈለው፣ ወይም

ለ) ለመዘግየቱ ምክንያት የሆነው የመንግሥት ሠራተኛው ራሱ ከሆነ ያለደመወዝ ክፍያ፣ እግዱ እስከ አንድ ወር ድረስ እንዲራዘም የመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሊወስን ይችላል፡፡

7/ ከሥራና ደመወዝ ታግዶ የቆየ የመንግሥት ሠራተኛ ከሥራ እንዲሰናበት ወይም በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት ደመወዙ እንዲከፈለውና ወደ ሥራው እንዲመለስ ሳይደረግ መደበኛውም ሆነ የተራዘመው የዕግድ ጊዜ ከተጠናቀቀ የሥራና የደመወዝ እግዱ ተነስቶ የዲስፐሊን ክሱ መታየት ይቀጥላል፤ ሆኖም ለመዘግየቱ ምክንያት የሆኑ የኮሚቴ አባላትና የሥራ ኃላፊዎች በዲስፐሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

### 4.6. የይርጋ ጊዜ

1/ ቀላል የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈፀመ የመንግሥት ሠራተኛ የፈጸመው ጥፋት ከታወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር እርምጃ ካልተወሰደበት በዲስፐሊን ተጠያቂ አይሆንም፤ ሆኖም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እርምጃ ያልወሰደው የሥራ ኃላፊ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2/ በወንጀል ጭምር የሚያስጠይቅ ከባድ የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ የወንጀሉን ክስ ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፐሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

3/ በወንጀል የማያስጠይቅ ከባድ የዲስፐሊን ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት የፈጸመ የመንግሥት ሠራተኛ የደንብ መተላለፍን ክስን ለማቅረብ በወንጀል ሕጉ በተደነገገው የይርጋ ጊዜ ውስጥ በዲስፐሊን ካልተከሰሰ በጥፋቱ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገጉት የዲስፐሊን ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜያት ቢኖሩም የዲስፐሊን ክስ ለማቅረብ ኃላፊነት ያለበት የሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ጥፋት መፈጸሙን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር ውስጥ ክሱን ካላቀረበ በዲስፐሊን ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

5/ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ መብቶቹን ለሚመለከተው አካል በስድስት ወር ውስጥ ካላቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

**4.7. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት**

**ቅሬታ**፡- ለዚህ ንኡስ ክፍል አፈጻጸም "ቅሬታ" ማለት የመንግስት ሠራተኛ ከቅርብ ኃላፊው ወይም ከሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ጋር በሚደረገው ውይይት ሊፈታ ያልቻለና በመደበኛ የማጣራት ሂደት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው አቤቱታ ነው፡፡

**4.8. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ዓላማ**

የመንግሥት ሠራተኞች ቅሬታ አቀራረብና አፈታት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1/ ለቅሬታዎች አፋጣኝ መፍትሔ የመስጠት፤

2/ ለቅሬታዎች መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ ስህተቶችንና ድክመቶችን የማረም፤ እና

3/ ሁሉንም የመንግሥት ሠራተኞች በእኩልነት ለማስተናገድ የሚያስችል እና ፍትሐዊ የሆነ አሠራር በማስፈን የሰመረ የሥራ ግንኙነት የማዳበር፡፡

**4.9. የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋም**

ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የመንግሥት ሠራተኞች የሚያቀርቡትን ቅሬታ እየተቀበለ በማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋም አለበት፡፡

**4.10. የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴው ተግባር**

የቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ከሚከተሉት ጋር በተያያዘ የመንግሥት ሠራተኛው የሚያቀርባቸውን ቅሬታዎች እያጣራ የውሣኔ ሀሣብ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፤

1/ ከሕጎችና መመሪያዎች አተረጓጎም ወይም አፈጻጸም፤

2/ ከመብቶችና ጥቅሞች አጠባበቅ፤

3/ ከሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ሁኔታዎች፤

4/ ከሥራ ምደባና ደረጃ አሰጣጥ፤

5/ ከሥራ አፈጻጸም ምዘና፤

6/ በሥራ ኃላፊ ከሚፈጸሙ ተገቢ ያልሆኑ ተፅዕኖዎች፤

7/ በአዋጅ 1064/2010 አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) እና (ለ) በተመለከቱት መሠረት ከሚወሰዱ የዲስፕሊን እርምጃዎች፤

8/ የሥራ ሁኔታዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች፡፡

**4.11. የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ፍርድ ቤት**

1/ የመንግሥት ሠራተኞች በአዋጅ 1064/2010 አንቀጽ 81 መሰረት የሚያቀርቡትን የስራ ክርክር አይቶ የሚወስን አስተዳደር ፍርድ ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2/ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚቀርቡለትን ይግባኞች መርምረው ውሳኔ የሚሰጡ ችሎቶች ይኖሩታል፡፡

3/ እያንዳንዱ ችሎት በሚኒስትሩ የሚሰየሙ አንድ ሰብሳቢና ሁለት አባላት ያሉት ዳኞች ይኖሩታል፡፡

4/ የአስተዳደር ፍርድ ቤት ዳኞች ሥራቸውን ስለሚሠሩበት ሁኔታ፣ መጠበቅ ስለሚገባቸው ሥነ-ምግባር፣ እና ሌሎች ሁኔታዎች በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**4.12. የአስተዳደር ፍርድ ቤት ሥልጣንና አሠራር**

1/ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ፣

ሀ) የሚቀርቡለትን ጉዳዮች በዳኝነት የማየትና ትዕዛዝና ውሳኔ የመስጠት፣

ለ) የመንግሥት ሠራተኛ ውሳኔ ተሰጥቷል ብሎ በቃለ መሃላ አስደግፎ የሚያቀርበውን ይግባኝ ተቀብሎ የማየት፣ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

2/ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚሰጣቸው ትዕዛዞችና ውሳኔዎች እንደ ማናቸውም የፍትሐብሔር ፍርድ ቤት ትዕዛዞችና ውሳኔዎች ይቆጠራሉ፡፡

**4.13. በአስተዳደር ፍርድ ቤት ስለሚታዩ ጉዳዮች**

የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሚከተሉትን ጉዳዮች አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፤

1/ ከሚከተሉት ጋር በተያያዘ በመንግሥት ሠራተኞች የሚቀርቡለትን ይግባኞች፤

ሀ) ከሕግ ውጪ ከሥራ መታገድ ወይም አገልግሎት መቋረጥ፤

ለ) ከከባድ የዲስፕሊን ቅጣት ውሳኔ፤

ሐ) ከሕግ ውጪ የደመወዝ ወይም ሌሎች ክፍያዎች መያዝ ወይም መቆረጥ፤

መ) በሥራ ምክንያት ከደረሰ ጉዳት የመነጨ መብት መጓደል፤

ሠ) በአዋጅ 1064/2010 አንቀጽ 77(7) ከተመለከተው በስተቀር በቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ታይተው ውሳኔ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች፤

ረ) የሥራ መልቀቂያና የአገልግሎት ማስረጃ ለማግኘት ከቀረበ ጥያቄ፤

2/ ጊዜያዊ ሠራተኞችና በማቋቋሚያ ሕጋቸው የመንግስት ሠራተኞች ሕግ መሠረታዊ ዓላማዎችን በመከተል በራሳቸው የውስጥ መመሪያ ሠራተኞቻቸውን እንዲያስተዳድሩ የተፈቀደላቸው መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሠራተኞች የሚያቀርቧቸውን ይግባኞች፡፡

3/ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ይግባኝ የተባለበትን አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመረመረ በኋላ ውሳኔውን ለማጽናት፣ ለመሻር ወይም ለማሻሻል ይችላል፡፡

4/ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በሰጠ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ የውሳኔን ግልባጭ ለይግባኝ ባዩ ወይም ለመስሪያ ቤቱ ተወካይ እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡

5/ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በፍሬ ነገር ክርክር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤ ሆኖም የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ የሚከራከር ወገን የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በደረሰው በ60 ቀን ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

**4.14. የውሳኔ አፈጻጸም**

1/ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ በደረሰው በአስር የስራ ቀናት ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡

2/ በአዋጅ 1064/2010 አንቀጽ 81(3) እና (4) መሠረት ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ እስከ 30 ቀን ድረስ አልተፈጸመልኝም በማለት የውሳኔው ተጠቃሚ ሲያመለክት የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን እንዲያስፈጽምለት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይመራለታል፡፡

3/ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ያላስፈጸመው የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በመስሪያ ቤቱና በሠራተኛው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡

# ምዕራፍ፡- ሦስት

## የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞች የሥነ-ምግባር መመሪያ

ክፍል አንድ ፡- **ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**አንቀጽ 1-አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞች የሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር ----- ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2- ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

1. «ዩኒቨርሲቲ» ማለት ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ነዉ፡፡

2. «ኮሚሽን» ማለት የፌዴራል ስነ - ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ነዉ፡፡

3. «የበላይ ስራ አመራር» ማለት የዩኒቨርሲቲዉ ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች ማዕረግ ያለዉ ነዉ፡፡

4. «ዲን» ማለት ዩኒቨርሲቲዉ የፋካሊቲና ት/ቤት ኃላፊዎች ማለት ነዉ፡፡

5. «መምህር» ማለት በዩኒቨርሲቲዉ ዉስጥ በቋሚነትና በኮንትራት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰዉ ነዉ፡፡

6. «መመሪያ» ማለት የዩኒቨርሲቲዉ የአካዳሚክ ዘርፍ ሰራተኞች የሥነ ምግባር መመሪያ ማለት ነዉ፡፡

7. «ቤተሰብ» ማለት የዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ዘርፍ ሰራተኛዉ ሚስት፤ ባልና ልጆች እንዲሁም በሰራተኛዉ ስር የሚተዳደሩ ሌሎች ሰዎች ናቸዉ፡፡

8. «የቅርብ ዘመድ» ማለት የአካዳሚክ ዘርፍ ሰራተኛዉ እስከ 3ኛ ደረጃ የሚቆጠር የስጋ ወይም የጋብቻ ዘመድ ነዉ፡፡

9. «ተገቢ ያልሆነ ባህሪ/ተግባር» ማለት ከዩኒቨርሲቲዉ አሰራርና ደንብ እንዲሁም ተቀባይነት ካለዉ ልማዳዊ አሰራር ጋር የሚቃረን ወይም የማይጣጣም ማንኛዉም ዓይነት ድርጊት ወይም ባህሪ ማለት ነዉ፡፡

10. «የስነ ምግባር ብልሹነት» ማለት በዚህ ደንብ ዉስጥ የተጠቀሱትን የስነ ምግባር መርሆችን ወይም እሴቶችን የሚቃረን ድርጊት ወይም ባሕሪይ ነዉ፡፤

11. «ሀብት» ማለት የዩኒቨርስቲው የበላይ የስራ አመራሩ የፋካሊቲ ወይም ት/ቤት ዲኑ፤የዲፓርትመንት ኃላፊው፤ ወይም የአካዳሚክ ዘርፍ ሰራተኛዉ ወይም የቤተሰቡ ማንኛዉም ገቢ፤ ቁጠባ፤ ኢንቨስትመንት፤ወይም የመሬት ይዞታ ወይም ሌላ ንብረት ነዉ፡፡

12. «ገቢ» ማለት ደመወዝ፤ ከግል ድርጅት፤ ሽርክና ከአክሲዮን የሚገኝ ትርፍ፤ የሎተሪ ገቢን፤የቁጠባ ገቢንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፡፡

13. «የጥቅም ግጭት» ማለት የአካዳሚክ ዘርፍ ሰራተኛዉ ወይም የቤተሰቡ ወይም የቅርብ ዘመዱ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከመደበኛዉ ስራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ወይም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሲሆን ነዉ፡፡

14. «ጥቅምን ማሳወቅ» ማለት በስራዉ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያደርግ ይችላል ወይም ያደርጋል ተብሎ የሚገመት የአካዳሚክ ዘርፍ ሰራተኛዉ ወይም የኃላፊዉ ወይም የቅርብ ዘመዱን የፋይናንስ ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅምን ማሳወቅ ነዉ፡፡

15. «ጥቅምን ማስመዝገብ» ማለት የአካዳሚክ ዘርፍ ሰራተኛዉን ወይም የኃላፊዉን ወይም የቤተሰቡን የፋይናንስ ጥቅምና ሀብትን በጽሁፍ አቅርቦ ማስመዝገብ ነዉ፡፡

16. «ስጦታ» ማለት ለዩኒቨርሲቲዉ ሰራተኛ ከስራዉ ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ወይም የተሰጠ ዋጋ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለዉ ማንኛዉም ነገር ነዉ፡፡

17. «መስተንግዶ» ማለት ለዩኒቨርሲቲዉ ሰራተኛና ኃላፊ ወይም ለቤተሰቡ በስራዉ ላይ እያለ የሚደረግለት ወይም የተደረገለት ነጻ የምግብ፤ የመጓጓዣ፤የሆቴል የመዝናኛ ወይም ሌላ ዓይነት አገልግሎት ነዉ፡፡

18. «ጥቆማ ማቅረብ ወይም ሪፖርት ማድረግ» ማለት፤ በዩኒቨርሲቲዉ ዉስጥ የተፈጸመዉን ሙስና ብልሹ አሰራርና የስነምግባር ግድፈቶችን አስመልክቶ ለስነ ምግባር መከታተያ ክፍል ወይም ለኮሚሽኑ በአካል ወይም በስልክ ወይም በጽሁፍ ወይም በሌላ በማንኛዉም መንገድ የሚቀርብ መረጃ ወይም የሚሰጥ አስተያየት ነዉ፡፡

19. «የስነምግባር መከታተያ ክፍል» ማለት በዩኒቨርሲቲዉ የስነ ምግባር ሁኔታን የሚያስተባብርና የሚያማክር አካል ነዉ፡፡

20. «የስነምግባር መኮንን» ማለት በደንብ ቁጥር 144/2000 የተቋቋመ የስነምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያ ነዉ፡፡

**አንቀጽ 3-የተፈጻሚነት ወሰን**

*ይህ የሥነ-ምግባር መመሪያ የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡በዚህ መመሪያ የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኛ ማለት እንደሁኔታው በዘርፉ የበላይ ኃላፊውንም ያጠቃልላል፡፡*

**አንቀጽ 4- የፆታ አገላለጽ**

*በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያጠቃልላል፡፡*

**አንቀጽ 5- የሥነ-ምግባር መመሪያው ዓላማዎች፣**

1. የሥነ-ምግባር ግደፈቶች እንዳይፈጸሙ ማስገንዘብ፣ ተፈጽመው ሲገኙ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፡፡
2. በዩኒቨርሲቲው የግልጽነትና የተጠያቂነት ባህል በማዳበር አድልዎ የሌለበት መልካም አስተዳደር በመገንባት ለሀገርና ለህዝብ ተቆርቋሪ የሆኑ ዜጐች ማፍራት፡፡

3. የህዝብ አገልጋይነትን ባህል በማዳበር ለህብረተሰቡ ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት መስጠት፡፡

4. በሥነ-ምግባር የታነፀ የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኛና ኃላፊ ማፍራት፣መልካም

ሥነ-ምግባር በማስፈን ውጤታማ ሥራ እንዲሠራ ማስቻል፡፡

**አንቀጽ 6- ኃላፊነት**

1. የዩቨርሲቲው የበላይ ኃላፊና የአካዳሚክ ዘርፍ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን የሥነ-ምግባር መመሪያ በሚገባ አውቀውት በሥራ ላይ ለማዋል እንዲችሉ የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞችን የማስተማርና የማሣወቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

2. የዩኒቨርሲቲዉ የአካደሚክ ዘርፍ መሪዎች ይህንን መመሪያ የመፈጸምና የመከታተል ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡

3. የዩኒቨርሲቲዉ የአካደሚክ ዘርፍ ሠራተኞችም ይህንን መመሪያ የመፈጸም ኃላፊነት አለባቸዉ፡፤

4. የዩኒቨርሲቲዉ የአካዳሚክ ዘርፍ የሥራ መሪዎችና ሠራተኞች በዩኒቨርሲቲዉ ውስጥ ከሥነ-ምግባር ጥሰት፣ሙስናና ብልሹ አሠራር ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ለዩኒቨርሲቲዉ የበላይ ኃላፊ፣ ለሥነ-ምግባር መከታታያ ክፍል ወይም ጉዳዩ ከባድ በሆነ ጊዜ ለኮሚሽኑ የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

5. የሥነ-ምግባር መኮንኑ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን የሥነ-ምግባር መርሆችን አፈጻጸም በሚመለከት የዩኒቨርስቲው የበላይ ሀላፊ የአካዳሚክ ዘርፍ ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን የማማከር፣ የማስተማርና በዩኒቨርሲቲዉ ዉስጥ ስላለው መልካም የሥነ-ምግባር ሁኔታ በየጊዜው ለበላይ ኃላፊው ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>፡-አጠቃላይ የሥነ-ምግባር መርሆዎችና የዲስፐሊን ጥፋቶች፣

ማንኛውም የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞችና ኃላፊዎች፡-

**አንቀጽ 7- ቅንነት /Integrity/**

1. የተጣለባቸውን የሙያ ግዴታ የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ በየኒቨርሲቲው ላይ እምነት እንዲኖረው ሊያደርግ በሚችል መልኩ መስራትና መምራት አለባቸው፡፡

2. መልካም ሥነ-ምግባር በማሳየት ሥራቸውን በከፍተኛ ሙያዊ ብቃት ጥንቃቄና ትጋት ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

3. ከህግና ከመመሪያ ውጭ ከመስራት፣ተገቢ ካልሆነ አድራጎትና ከስነ-ምግባር ብልሹነት መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡

4. በማህበራዊና በግል ህይወታቸው ህብረተሰቡ በዩኒቨርሲቲው ላይ ያለውን አመኔታና አክብሮት ሊያስጠብቅ ወይም ሊያጐለብት በሚችል መልኩ በመስራት የዩኒቨርሲቲውን ዝናና ክብር ማስጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡

5. የቅርብ ኃላፊዎቹ የሚሰጡትን ትዕዛዝ ከህግና ከቅጥር ኮንትራት ውል ስምምነት ጋር እስካልተቃረነ ድረስ መቀበልና ተግባራዊ ማድረግ፡፡

6. መርሆውንና በመርሆው ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ/ የዩኒቨርሲቲውን ዝና የሚጐዳ ወይም ማህበረሰቡ በዩኒቨርሲቲው ላይ የሚኖረውን እምነት ዝቅ የሚያደረግ ባህሪይ ማሳየት ወይም ተግባር መፈፀም፤

ለ/ አቅሙ እየፈቀደ በስራው ላይ ተገቢውን ጥረት አለማድረግ

ሐ/ ሱስ በሚያስይዝ መድሐኒት ወይም በአደንዛዥ እጽ ሱስ በመመረዝ ወይም በልማዳዊ መጠጥ ተፅዕኖ ምክንያት ስራን ማከናወን አለመቻል ወይም በስራ ላይ በደል ማድረስ፤

መ/ ሱስ በሚያስይዝ መድሐኒት ወይም በአደንዛዥ እጽ ሱስ ወይም ጫትና መሰል እፆችን ወደ ዩኒቨርሲተው ቅጥር ግቢ ይዞ መግባት ወይም እንዲገባ መርዳት ወይም በቢሮ እና በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሲጋራ ማጨስ፣

ሠ/ የሥራ ባልደረባን ወይም ተማሪን ለወሲብ ማሰጨነቅ፣ማስገደድ፤ ፆታዊ ጥቃት መፈፀም ወይም መሞከር አስገድዶ መድፈር ወይም ለሌሎች ሰዎች ሁኔታዎችን ማመቻቸት

ረ/ ስራን ሙያው በሚጠይቀው የሥነ-ምግባር ደረጃ አለማከናወን፤

ሰ/ ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመግባባት መስራት ባለመቻል በስራ ሂደት ላይ እንቅፋት መሆን፤

ሸ/ ከቅርብ ኃላፊዎች የተሰጠውን ሥራ አለመቀበል፡፡

**አንቀጽ 8- ታማኝነት**

1. ለሀገራቸውና ለፌደራሉ ህገ-መንግስት ታማኝ መሆን አለባቸው፡፡
2. ስራቸውን ህግንና ዩኒቨርሲቲው የሚያወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ ማከናወን ይኖርባቸዋል፤የመንግስት ንብረት እና የሥራ ሰዓት በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል ይገባቸዋል፡፡
3. የስራ ባልደረቦቻቸውን ህገ-ወጥ ድርጊት ለቅርብ ኃለፊዎቻቸዉ ወቅቱን ጠብቀው ማሳወቅ አለባቸው፡፡
4. የመንግስትን ገንዘብ ንብረትና የሥራ ሰዓት ለግል ጥቅማቸው ማዋል የለባቸውም፡፡
5. የተሰጠውን ወይም የተረከበውን በስሩ የሚገኙ ንብረቶችን በአግባቡ መያዝና መጠበቅ አለባቸው፡፡
6. ከሙያው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሥነ ምግባር ደንቦችን መተግበር፡፡
7. መርሆውንና በመርሆው ስር የተጠቀሰቱን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

   ሀ/ ለተመሳሳይ ስራ የተመደበ የሥራ ባልደረባን የብቃት ማነስ እያወቀ ለቅርብ የሥራ ኃላፊው አለማሳወቅ

   ለ/ የሥራ ባልደረባን ህገ-ወጥ ድርጊት ወይም የሥነ-ምግባር ጉድለት ወይም ተገቢ ያልሆነ አድራጐት ለስራ ኃላፊው ወይም ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል አለማሳወቅ፡፡

   ሐ/ አንድ ስራ እንዳይሰራ ወይም ውሳኔ እንዳይፈፀም እንቅፋት መፍጠር ወይም ሥራ እንዳይሰራ ከሚያውኩ ሰዎች ጋር መተባበር፤

   መ/ በዩኒቨርሲቲው ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መረጃ ሆን ብሎ መግለጽ፤

   ሠ/ በህግ አግባብ ፈቃድ ከተሰጣቸው ሰራተኞችና ኃላፊዎች ውጭ ወይም ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ፈቃድ ውጪ በዩኒቨርሲቲው አገልግሎት ወይም ንብረት ወይም ገንዘብ ያለአግባብ መጠቀም ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙ ማድረግ ወይም ለግል ጥቅም ማዋል፡፡

   ረ/ በዩኒቨርሲቲው የሥራ ሰዓት የግል ወይም የሌላ ሰው ስራን ማከናወን፤

   ሰ/ ያለበቂ ምክንያት በሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለሚመለከተው አመራር ወይም አካል በወቅቱ አለማሳወቅ፤

   ሸ/ በዩኒቨርሲቲው ንብረት እና ሀብት ላይ የስርቆት ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት መፈፀም

   ቀ/ በዩኒቨርሲቲው ንብረት ላይ ሆን ብሎ ጉዳት ማድረስ

   በ/ ከዩኒቨርሲቲው የተረከበውን ንብረት በአግባቡ አለመያዝና በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ

   ተ/ ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር አለመከተል ወይም ከሥነ-ምግባር ውጪ መሥራት፡፡

**አንቀጽ 9- ግልጽነት**

1. በአሰራራቸው ግልጽ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ሊያውቀው የሚገባውንና በምስጢር ያልተያዘን መረጃ መደበቅ የለባቸውም፡፡ አንድ መረጃ በምስጢር ሊጠበቅ የሚገባው አግባብ ባለው ህግ ወይም በበላይ የስራ አመራር ውሳኔ መሰረት ምስጢር የተባለ ከሆነ ብቻ ነው፡፡
2. ለሚሰጧቸው ውሳኔዎች እና አገልግሎቶች ግልጽ መሆንና ውሳኔያቸውን ወይም የሚሰጡትን አገልግሎት አስመልክቶ ከተጠቃሚው ጥያቄ ሲቀርብላቸው መረጃው በሚስጢር የሚጠበቅ ካልሆነ በቀር ሕግና መመሪያን ተከትለው ተገቢውን ማብራሪያ ወይም ምላሽ መስጠት አለባቸው፡፡
3. የተሰጠውን የማስተማር ሥራ ዕለት በዕለት በአግባቡ መወጣትና ተቀባይነት ባለው ምክንያት ከሥራ በሚቀርበት ጊዜ አስቀድሞ ለቅርብ ኃላፊው ማሳወቅና ከዚያም በኃላ አሰፈላጊውን የማካካሻ የማስተማር ሥራ ማከናወን፡፡
4. የተማሪዎችን የፈተና ውጤት ለተማሪዎች በግልጽ ጊዜውን ጠብቆ ማሳየት፡፡
5. መርሆውንና በመርሆው ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም የስቀጣል፡፡

   ሀ/ ሕጋዊ ለሆነ ጥያቄ በእጁ የሚገኘውን ምስጢር ያልሆነንና ለዩኒቨርሲቲው ማህረሰብ ግልጽ እንዳይደረግ ያልተከለከለን መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን

   ለ/ ለሚያስተላልፈው ውሳኔ ተገቢውን ማብራሪያ ወይም ምክንያት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን

ሐ/ ለግምገማ የሚያስፈልግ መረጃ አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ በወቅቱ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፡፡

መ/ የተማሪውን ፈተና ውጤት በወቅቱ ለማሳየትና ቅሬታን ለማስተናገድ ፈቃደኛ አለመሆን፡፡

ሠ/ ከሥራ ገበታው ላይ ሲቀር ቀድሞ ለቅርብ ኃላፊው ያለማሳወቅና የቀረበትን የማስተማር ጊዜ ያለማካካስ፡፡

## አንቀጽ 10. ሚስጥር ጠባቂነት

1. በስራቸው ምክንያት ያወቋቸውን ምስጢራዊ መረጃዎች መጠበቅ አለባቸው፤ምስጢራዊ ያልሆነ ወይም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ሊያውቀው የሚገባውን መረጃ መግለጽ ይችላል፡፡
2. ዩኒቨርሲቲውን ከለቀቁ ወይም ወደ ሌላ ስራ ከተዛወሩ በኋላም ቢሆን በስራቸው ምክንያት ያወቋቸውን ምስጢራዊ መረጃዎችንም የመጠበቅ ግዴታ አለባቸዉ፡፡ ጥፋት ለማጋለጥ ለሚመለከተዉ አካል ሚስጢራዊ መረጃም ማሳወቅ እንደ ሚስጢር ማባከን አይቆጠርም፡፤
3. መርሆንና በመርሆው ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም የስቀጣል፡፡
   ሀ/ ያልተፈቀደን ወይም ሚስጥራዊ መረጃን በማናቸውም ሁኔታ ሆን ብሎ መግለጽ፤

   ለ/ ያልተፈቀደን ወይም ሚስጥራዊ መረጃን በማንኛዉም ሁኔታ በቸልተኝነት መግለጽ፤

   ሐ/ ሚስጢራዊ መረጃን ለግል ጥቅም ማዋል፤

   መ/ በዩኒቨርሲቲው አሰራር ወይም በተገልጋይ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መረጃን ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት ሆን ብሎ መግለጽ

   ሠ/ የተማሪ ፈተና አግባብነት በሌለውና ከፈተናው ቀን ቀድሞ የተዘጋጀውን ፈተና እንዲወጣ ማድረግ፡፡

## አንቀጽ 11. ሐቀኝነት

1. በመንግስት ሥራቸው አጋጣሚ የገቡትን ቃል መጠበቅና ማክበር አለባቸው፡፡በተጨማሪ ከሙስና፣ከማታለል እና በስልጣን ከመነገድ የፀዱ መሆን አለባቸው፡፡
2. ከስራቸው ጋር በተያያዘ ማንኛውም ዓይነት ስጦታ ወይም መስተንግዶ መቀበል የለባቸውም፡፡
3. መርሆውን ወይም በመርሆው ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፤
   ሀ/ ማጭበርበር፣ በስልጣን መነገድ፣ በስልጣን አለአግባብ መገልገል፣ ሰነድ የተማሪዎችን ውጤት መደለዝ ወይም የዩኒቨርሲቲውን አርማና ማህተም ለሕገ-ወጥ ድርጊት መጠቀም፣ አታላይነት፣ ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፤ወይም ሌሎች የሙስና ወንጀሎችን መፈፀም

   ለ/ ሀሰተኛ ወይም ተገቢ ያልሆነ የአበል ክፍያ ጥያቄ ማቅረብ፤

   ሐ/ ከስራው ጋር በተያያዘ ስጦታ ወይም መስተንገዶ መቀበል፤

   መ/ በስራ ሂደት ላይ ለተፈጠሩ ችግሮች ቅን ልቦናን በሚቃረን ሁኔታ ጥቆማ ማቅረብ፤

## አንቀጽ 12. ተጠያቂነት /Accountability/

1. ለሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ለሚያከናውኗቸው ስራዎች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ለሚያከናውኗቸው ተግባራትም ተገቢውን ምክንያት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
2. የመንግስትን ፖሊስ መፈፀም ወይም ማስፈፀም አለባቸው፡፡
3. ተገቢው ጥያቄ ሲቀርብላቸው የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኞች ሥራቸውን በአግባቡ ስለማከናወናቸውና ኃላፊነታቸውን ስለመወጣታቸው አስፈላጊውን ማብራሪያ መስጠት ይገባቸዋል፡፡
4. ከት/ክፍሉ ወይም ፋካሊቲው የሚሰጠውን ሥራ በአግባቡ ማደራጀት፣መምራትና ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡
5. ተማሪዎችን ከሚያሸማቅቅ ማንኛውም ዓይነት ተግባርና ሁኔታ መቆጠብ ይጠበቅበታል፡፡
6. የሚያስተምረውን ኮርስ አስቀድሞ ለሚመለከተው ኃላፊ ሳያሳውቅ ለሌላ ሰው አሣልፎ መስጠት አይገባም፡፡
7. እውቀትን የሚያስፋፋና ለሀገሪቱ እድገት የሚጠቅሙትን ምርምሮች በሰለጠነበት የት/መስክ ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡
8. ዩኒቨርሲቲው በሚፈልገው በራሱ የት/መስክ እንቅስቃሴዎችን በማደራጀት፣ በመምራትና በማከናወን መሳተፍ ይጠበቅበታል፡፡
9. የዩኒቨርሲቲውን ሥራ እንደ ሙሉ ጊዜ ተግባሩ ማከናወን ወይም መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

10. ፈተናዎችንና ውጤቶችን በወቅቱ ለት/ክፍሉና ለሬጅስትራር ጽ/ቤት ማስገባት ይጠበቅበታል፡፡
11. ስለሚሰራው የምርምር ሥራና ስለሚያስተምረው ኮርስ ተገቢውን ሪፖርት ለሚመለከተው የአካዳሚክ ዘርፍ በጊዜ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡
12. የተሰጠውን ሙሉ የማስተማር ስራ በተሰጠው ፕሮግራም መሠረት ማከናወንና ማጠናቀቅ ይጠበቅበታል፡፡
13. ከተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደትና ከውጤት ጋር ተያያዥነትና አግባብነት ያላቸው ጥያቄዎች ሲቀርቡ መቀበልና ማስተናገድ ይጠበቅበታል፡፡
14. ማንኛውም የፈተና ወረቀት መምህሩ የፈተናውን ውጤት ካስገባ በኃላ ለትም/ ክፍሉ ቆጥሮ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡
15. የትም/ክፍል ኃላፊዎች ከየመምህራን የፈተና ወረቀት ተቀብለው ቢያንስ ለ6 ወራት በጥንቃቄ መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡
16. መርሆውንና በመርሆው ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ/ ስላከናወናቸው ስራዎች ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ሪፖርት አለማቅረብ

ለ/ ስላከናወናቸው ስራዎች ለሚመለከተው አካል ሆነ ብሎ የሚያሳስት ወይም ትክክል ያልሆነ ሪፖርት ማቅርብ

ሐ/ ስላከናወናቸው ስራዎች ለሚመለከተው አካል በቸልተኝነት የሚያሳስት ወይም ትክክል ያልሆነ ሪፖርት ማቅረብ፤

መ/ የተሰጠውን ሥራ ያለበቂ ምክንያት በወቅቱ አለማከናወን፣

ሠ/ ያለፈቃድ ወይም ስልጣን ሳይኖረው በኮምፒውተር የተያዘ ዳታን ማጥፋት ወይም መለወጥ ወይም የተሳሳተ መረጃ ማስገባት፣

ረ/ ኃላፊነት እያለበት ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎችን ሲጠየቅ ያለበቂ ምክንያት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ወይም በወቅቱ አለመስጠት

ሰ/ ኃላፊነት እያለበት ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎችን ሲጠየቅ ሆነ ብሎ የተሳሳተ መረጃ መስጠት፣

ሸ/ የመንግስትን ፖሊሲ ሆን ብሎ ለመፈጸም ወይም ለማስፈጸም ፈቃደኛ አለመሆን፤፤

ቀ/ ተማሪዎችን በተለያየ መልኩ በነጻነት እንዳይማሩ ማሸማቀቅ፤

በ/ የሚያስተምረዉን ኮርስ አስቀድሞ ለሚመለከተዉ ኃላፊ ሳያሳዉቅ ለሌላ ሰዉ አሳልፎ መስጠት፤

ተ/ የተሰጠዉን የዩኒቨርሲቲዉን ስራ እንደ ሙሉ ጊዜ ተግባሩ አለማከናወን፤

ቸ/ ፈተናዎችንና ዉጤቶችን በወቅቱ ለሚመለከታቸዉ ክፍሎች አለማስገባት፤

ነ/ ከተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደትና ከዉጤት ጋር የተያያዙ አግባብነት ያላቸዉን ጥያቄዎች ሲያቀርቡ አለመቀበልና ለማስተናገድ ያለመፈለግ፤

ኘ/ ዉጤቶችን ካስገባ በኃላ የፈተና ወረቀቶችን ቆጥሮ ለትምህርት ክፍል ኃላፊ አለማስገባት፤

አ/ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች የፈተና ወረቀቶችን ከመምህራን ተቀብለዉ ቢያንስ ለ6 ወራት በጥንቃቄ ያለማስቀመጥ፤

**አንቀጽ 13. የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም**

1. የግል ጥቅማቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውን፣የሌላ ሶስተኛ ወገን ወይም ቡድን ሳይሆን የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ጥቅም መሰረት በማድረግ ስራቸውን ማከናወን አለባቸው፡፡
2. በህግ ግዴታ እያለባቸው የራሳቸውን፣ የቅርብ ዘመዶቻቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ሀብትና የገንዘብ ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ አለባቸው፡፡
3. ከመደበኛ ስራቸው ጋር ሊጋጭ የሚችል ማንኛውም ዓይነት ጥቅም ማሳወቅና እንዲሁም ግጭቱን ማስወገድ አለባቸው፡፡
4. መርሆውንና በመርሆው ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡

ሀ/ የግል ወይም የተወሰኑ ቡድኖችን ጥቅም ከዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ጥቅም ማስቀደም

ለ/ በህግ ግዴታ እያለበት ጥቅምን ሆነ ብሎ አለማሳወቅ

ሐ/ በሕግ ግዴታ እያለበት ጥቅምን በቸልተኝነት አለማሳወቅ

መ/ በሕግ ግዴታ እያለበት የራሱንና የቤተሰቡን ሀብት ለማስመዝገብ ፈቃደኛ አለመሆን

ሠ/ በሕግ ግዴታ እያለበት ሆን ብሎ ያልተሟላ ወይም ሀሰተኛ የሀብት ምዝገባ ማድረግ

ረ/ በሕግ ግዴታ እያለበት በቸልተኝነት ያልተሟላ ወይም ሀሰተኛ የሀብት ምዝገባ ማድረግ

ሰ/ ከዩኒቨርሲቲው እውቅና ውጭ በዩኒቨርሲቲው የሥራ ሰዓት በሌላ መ/ቤት ወይም ድርጅት ተቀጥሮ መስራት፤

### አንቀጽ 14. ሕጋዊ በሆነ ስልጣን መገልገል

1. የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በአግባቡ እንዲያገለግሉና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የተሰጣቸውን ስልጣንና ኃላፊነት ለዩኒቨርሲቲው በህግ ተወስኖ በተሰጠው የስልጣን ገደብ ውስጥ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡
2. አዋጅ፣ ደንብን ወይም መመሪያን መሰረት በማድረግ ስራቸውን ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡
3. በስልጣናቸው ያለአግባብ መገልገል የለባቸውም፡፡ ስልጣናቸውን የግል ጥቅም ለማግኘት ማዋል የለባቸውም፡፡
4. መርሆውንና በመርሆ ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡
   ሀ/ ከስልጣን በላይ መስራት ወይም በስልጣን አለአግባብ መገልገል ወይም በስልጣን መነገድ ወይም በወንጀል ህጉ ላይ የተቀመጡትን ተመሳሳይ ጥፋቶች በተሰጠው ስልጣን ላይ መፈፀም፤

   ለ/ ስራን በተገቢው ጥንቃቄ አለማከናወን፤

   ሐ/ በስራ ባልደረቦች ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና ማሳደር፤

### አንቀጽ 15. አድልዎ አለመፈፀም

1. አድልዎ በሌለበት ሁኔታ ተገቢና ፍትሃዊ በሆነ አኳኃን ውሳኔ የመስጠት ስራቸውን የማከናወን ግዴታ አለባቸው፡፡ በቀለም፣በዘር፣በብሔር/ብሔረሰብ፣በፆታ፣በቋንቋ፣በሃይማኖት፣በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ወይም አግባብነት በሌለው ምክንያት የተለየ እንክብካቤ ወይም ልዩነት ሳያደርጉ ስራቸውን ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡
2. ሕግን ብቻ መሰረት በማድረግ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡
3. መርሆውንና በመርሆው ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉት ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡
   ሀ/ የአንድን ጉዳይ ፍሬ ነገር መሰረት ያላደረገና አንድን ቡድን ወይም ግለሰብ የሚጠቅም ወይም የሚጐዳ አድሏዊ ምክር መስጠት፤

   ለ/ ከህግና ከመመሪያ ውጭ የሆነ ቅጥርና ዝውውር መፈፀም፣ ዕድገት፣ስልጠና ወይም የትምህርት እድል መስጠት፤

### አንቀጽ 16. ሕግ ማክበር

1. ለሕግ መገዛትና ለስራው አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ አዋጆችን፣ደንቦችን መመሪያዎችን መከተልና ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡
2. የዩኒቨርሲቲው የበላይ ስራ አመራርና የሥራ መሪዎች በሕጋዊ ስልጣናቸው የሚያስተላልፉትንም ተዕዛዞች የመፈፀም ኃላፊነት አለባቸው፤ሆኖም ህገ-ወጥ ትዕዛዝ መፈፀም የለባቸውም፡፡
3. የስራ መሪዎች ህገ-ወጥ ትዕዛዝ ወይም ተገቢ ያልሆነ መመሪያና ትዕዛዝ በስራቸው ላሉ የስራ መሪዎች ወይም ሰራተኞች ማስተላለፍ የለባቸውም፡፡
4. የበላይ አለቆቻቸው የሚሰጡትን መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ህገ-ወጥ ወይም ተገቢ ካልሆነ መመሪያውን ወይም ትዕዛዙን ለሰጠው ኃላፊ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡
5. በዩኒቨርሲቲው መመሪያና ፖሊሲ መሠረት ማስተማርና ሌሎች ገለጻዎችን ለተማሪዎች መስጠት ይኖርበታል፡፡
6. መርሆውንና በመርሆው ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡
   ሀ/ ሕጐችን ወይም የአሰራር ስርዓቶችን በመጣስ መስራት ወይም ሕጋዊ የሆኑ ትዕዛዞችን አለማክበር ወይም ሌሎች ሰራተኞች እንዳያከብሩ መገፋፋት ወይም ማበረታታት፤

   ለ/ የቅርብ የስራ ኃላፊውን ፈቃድ ሳያገኝ ከስራ መቅረት፤

   ሐ/ መቅረቱ በስራው ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርስ እያወቀ የቅርብ የስራ ኃላፊውን ፈቃድ ሳያገኝ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ከስራ መቅረት፤

   መ/ በስራ አከባቢ አምባጓሮ ወይም ጠብ መፍጠር ወይም ባለጉዳይን ወይንም ባልደረባን ወይንም የስራ ኃላፊን መስደብ ወይም መደባደብ ወይም የድሪጊቱ ተባባሪ መሆን፤

ሠ/ በማንኛውም ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት እና በጥፋቱም ምክንያት ለሥራው ተገቢ ሆኖ አለመገኘት፤

ረ/ ህግን ወይም ህጋዊ ትዕዛዝን ወይም የአሰራር ሥርአትን  አልያም የመንግስት ፖሊስ ባለመከተልና ባለማክበር ሆነ ብሎ በስራ ላይ በደል ማድረስ፤

ሰ/ የስራ መግቢያና መውጫ ሰዓትን አለማክበር ወይም ለቅርብ ኃላፊው ሳያሳውቁ እና ያለበቂ ምንያት ገብቶ መውጣት፤

ሸ/ በዩኒቨርሲቲው መመሪያና ፖሊስ መሠረት አለማስተማርና የተለያዩ ገለጻዎችን አለማድረግ፡፡

**አንቀጽ 17. ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት**

1. ባለጉዳዮች ተገቢውን አክብሮት በመስጠትና ትህትና በማሳየት ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡
2. ባለጉዳዮች ግራ ሊጋቡ፣ትዕግስት ሊያጡና ሊናደዱ ስለሚችሉ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ዘርፍ ሰራተኞች በትዕግስት ሊያስተናግዷቸው ይገባል፡፡
3. አንገብጋቢና አስቸኳይ ሁኔታዎች ተፈጥረው ተጨማሪ አካዳሚክና ሙያዊ ሥራ ከማህበረሰቡ ከማካካሻ ክፍያ ጋር ሲጠየቅ ተቀብሎ መፈፀም ይገባል፡፡
4. መርሆውንና በመርሆው ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡
   ሀ/ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መብቱን በሚመለከት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ፤

   ለ/ ለባለጉዳይ ተገቢውን ትህትና አለማሳየት ወይም እንዛ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆን፤

   ሐ/ ባለጉዳዮች ለሚያቀርቡት ጥያቄዎች ወቅታዊ  ምላሽ አለመስጠት ወይም ባለጉዳዮችን ያለአግባብ ማጉላላት፤

   መ/ ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት ጉዳዮችን ወይም አቤቱታዎችን ማዘግየት፤

   ሠ/ ከማህበረሰቡ ከማካካሻ ክፍያ ጋር ተጨማሪ ሥራ ሲሰጠዉ ተቀብሎ አለመፈጸም፤

**አንቀጽ 18. አርአያነት፤**

1. የመንግስትን ሥራ በሚያከናዉኑበት ጊዜና በማህበረሰቡ ዉስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ግንባር ቀደምና ምሳሌ በመሆን የሚጠበቅባቸዉን ከፍ ያለ የአርአያነት ባህሪ በማሳየት በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን መርሆዎች ማጎልበትና በተግባር እንዲተረጎሙ ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡

2. የኃላፊነት ስሜት የሚሰማቸዉ፤ የተሻለ ለዉጥን የሚደግፉ፤ የዩኒቨርሲቲዉን መልካም ስም የሚጠብቁና የአሰራር ባህል እንዲዳብር፤ መተማመን ስር እንዲሰድና ጸንቶ እንዲቆይ የሚያደርጉ መሆን አለባቸዉ፡፤

3. በሙያዉ አዲስና ዘመናዊ እዉቀት ለማግኘት የሚጥርና የሚያስተምርበትን የማስተማሪያ ቁሳቁስና ማስተወሻ በየጊዜዉ የሚያድስ ሊሆን ይገባል፡፡

4. ከዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ ጋር በመግባባትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግኑኝነትን የሚያሳድግ ሊሆን ይገባል፡፤
5. በዩኒቨርሲቲዉ ጉዳዮች ላይ አቅሙ የፈቀደዉን ያህል ንቁ ተሳትፎ ሊያደርግ ይገባል፤፤
6. ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ስልጣኔን በመያዝ ከሌሎች የዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ ጋር በመግባባትና በመከባበር ለመስራት ፈቃደኛ መሆን ይገባል፡፡
7. በተደነገጉ አዋጆች መሰረት ተጨማሪ ድጋፍ ለሴቶች፤ ለአካል ጉዳተኞችና ለሌሎች ተጎጂ አካሎች ተገቢዉን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
8. መርሆውንና በመርሆዉ ስር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈፀም ያስቀጣል፡፡
   ሀ/ ኃላፊነት እያለበት አግባብነት ያለውን የዩኒቨርሲቲውን አሰራርና  የስነ-  ምግባር መርሆዎች ለአዲስ ተቀጣሪ ሰራተኞች አለማሳወቅ

   ለ/ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ ወይም ሌሎች ተገልጋዮችን ወይም የስራ ባልደረቦችን መዝለፍ፣ማመናጨቅ ወይም መልካም ስነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ አለማስተናገድ፤

   ሐ/ ከበላይ ኃላፊዎች ወይም ከት/ ክፍል ተጠሪዎች የቡድንና የኮሚቴ ስራ እንዲሠራ ትዕዛዝ ሲሰጥ ያለበቂ ምክንያት ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆን፤

መ/ አቅሙ እየፈቀደ በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሣትፎ አለማድረግ፤

ሠ/ ድጋፍ ለሚመለከታቸው ተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ አለማድረግ፤

ረ/ ተማሪዎችን በማንኛውም ተግባርና ሁኔታ ማሸማቀቅ፤

ሰ/ የሚያስተምረውን ኮርስ አስቀድሞ ለሚመለከተው ኃላፊ ሳያሳውቅ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት፤

ሸ/ በምርምር ሥራዎች እና ዩኒቨርሲቲው ከእርሱ በሚፈልገው የተለያዩ የሙያ ድጋፍ ላይ ያለበቂ ምክንያት አለመሳተፍ፤

ቀ/ ሙሉ የስራ ጊዜዉን በዩኒቨርሲቲዉ ስራ ላይ አለማዋል፤

በ/ ፈተናዎችንና ውጤቶችን ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ አለማስገባት፤

ተ/ የተሰጠውን ሙሉ የማስተማር ሥራ በተሰጠው ፕሮግራም መሠረት አለማጠናቀቅ፤

ቸ/ ከመማር ማስተማር እና ከውጤት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቅሬታዎች ተቀብሎ አለማስተናገድ፣

ኀ/ የፈተና ወረቀቶችን ለት/ክፍል ገቢ ያለማድረግና ለ6 ወር በጥንቃቄ ጠብቆ ያለማቆየት

**<u>ክፍል ሦስት</u>፡-የዲሲፕሊን ጥፋትና እርምጃዎች፤**

**አንቀጽ 19. የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማና አፈጻጸም፤**

1. በዩኒቨርሲቲዉ መምህራንና ኃላፊዎች ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን ቅጣት ዓላማዉ፤

   ሀ/ በስነ ምግባር የታነጸ  ኃላፊና መምህራንን ለማፍራት፤

   ለ/ ኃላፊዎችም ሆኑ መምህራን የስነ ምግባር ግድፈት እንዳይፈጽሙ ለማስተማርና ፈጽመዉ ሲገኙም በማረም ተገቢዉን እርምጃ ለመዉሰድ፤ የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ከስራዉ ለማሰናበት ነዉ፡፡

2. በዩኒቨርሲቲዉ መምህራንና ኃላፊዎች ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን ቅጣት አፈጻጸሙ፤

   ሀ/ መምህራንና ኃላፊዎች ስራቸዉን በአግባቡ ባለመፈፀማቸው ወይም ማድረግ የማይገባቸውን በማድረጋቸው ስለ ጥፋታቸው በፍትሐብሔር ወይም በወንጀል ወይም በሁለቱም ህጐች ተጠያቂነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ላደረሱት ጥፋት ወይም የዲስፒሊን ጉድለት በዚህ የስነ-ምግባር መመሪያ መሠረት ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡፡

   ለ/ በዲስፒሊን ጥፋት የሚፈፀሙ ቅጣቶች ማናቸውም ፍ/ቤት የሚሰጠውን ውሳኔ ሳይጠብቁ ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 20. የዲስፒሊን ቅጣት ዓይነቶች**

1. **ቀላል የዲሲፒሊን ቅጣቶች**

   ሀ/ የቃል ማስጠንቀቂያ

   ለ/ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ

   ሐ/  እስከ አንድ ወር የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት

2. **ከባድ የዲሲፒሊን ቅጣቶች**

   ሀ/ ከአንድ ወር እስከ ሦስት ወር የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት

   ለ/ ከኃላፊነት ማንሳት

ሐ/ የአንድ ጊዜ የደረጃ ዕድገት ማገድ

መ/ ከስራ ማሰናበት

**አንቀጽ 21. ቀላል የስነ-ምግባር ግድፈቶች**

1. በዚህ መመሪያ በክፍል 2 አንቀጽ 7 ንኡስአንቀጽ 6/ሀ/ለ/ሐ/መ/ሠ/ረ/ሰ/ሸ/ አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 7 ሀ/ለ/ረ/ሰ/በ/ተ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 5.ሀ/ለ/ሐ/መ/ሠ/ አንቀጽ 10.ንዑስ አንቀጽ 3. ሀ/ለ/መ/ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ3 ለ/ሐ/መ/ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 16 ሀ/ለ/ሐ/መ/ ረ/ሸ/ቀ/በ/ተ/ቸ/ነ/ኘ/አ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 ለ/ሐ/ አንቀጽ15 ንዑስ አንቀጽ 3 /ሀ/አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 6 ለ/ሰ/ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 4 ሀ/ለ/ሠ/ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 8 /ሀ/ለ/ሐ/መ/ሠ/ረ/ሰ/ሸ/ቀ/በ/ቸ/ኀ/የተመለከቱትን ጥፋቶች መፈጸም ቀላል የዲስፒሊን ቅጣትን ያስከትላል፡፡ በሚል በዚህ መልኩ ይደነገጋሉ፡፡

**አንቀጽ 22. ከባድ የስነ-ምግባር ግድፈቶች**

1. በዚህ መመሪያ በክፍል 2፡ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 7,ሐ,መ,ሠ,ሸ,ቀ 10 ንዑስ አንቀጽ 3 ሐ/ሠ/ አንቀጽ 11፡ ንዑስ አንቀጽ 3፡ ሀ. አንቀጽ 12፡ንዑስ አንቀጽ 16 ሠ.ሰ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ፡4 ሀ,ለ,ሐ,መ,ሠ,ረ,ሰ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4/ሀ/አንቀጽ15 ንዑስ አንቀጽ3 /ለ/ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ6 /ሀ/ሐ/መ/ሠ/ረ/ሸ/አንቀጽ17 ንዑስ አንቀጽ4 /ሐ/መ/አንቀጽ18 ንዑስ አንቀጽ8/ተ/
2. በዚህ መመሪያ ቀድሞ የተቀጣ ሠራተኛ ወይም የሥራ ኃላፊ ሌላ ጥፋት እስካላጠፋ ድረስ የተወሰነበት ቅጣት፡-
   ሀ/ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከሆነ ከተቀጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር በኃላ

   ለ/ የገንዘብ ቅጣት ከማስጠንቀቂያ ጋር ከሆነ ከተቀጣበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኃላ

   ሐ/ በድስፒሊን ጉድለት የተቀጣ ሠራተኛ የጥፋተኝነቱ ሪኮርድ ሳይሰረዝለት እንደገና ከተቀጣ የኃለኛው የሪኮርድ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የቀድሞው ሪኮርድ የሚሰረዝበት ጊዜ ሲያበቃ ነው፡፡

   መ/ በደረጃ ማገድ ሊቆይ የሚችለው ለሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ብቻ ነው፡፡ሆኖም ከሥራ መሰናበትና የገንዘብ ቅጣቶች ተመላሽ አይሆንም፡፡ /እንደ ስምምነታችው ጊዜው ሊወሰን ይችላል፡፡/
3. በገንዘብ ያስቀጡ ቀላል የስነ-ምግባር ግድፈቶችን በተደጋጋሚ ጊዜ መፈፀም ከባድ የዲስፒሊን ቅጣትን ያስከትላል፡፡

**አንቀጽ 23. የዲስፒሊን እርምጃ አወሳሰድ**

1. ማንኛውም የዲስፒሊን እርምጃ አወሳሰድ ከሥራ ማገድ፣የቅሬታና የይግባኝ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት የሚመራው በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 እና በዲስፒሊን አፈጻጸም የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓትደንብ ቁጥር 77/94 መሠረት ይሆናል፡፡
2. የሥነ-ምግባር ግድፈት የፈፀመ ማንኛውም ሠራተኛ በዚህ የሥነ-ምግባር መመሪያና በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 በተደነገገው መሠረት በአንድ ጊዜ በተደራራቢነት ሊቀጣ አይገባውም፡፡
3. በስነ-ምግባር ግድፈት የተቀጣ ሠራተኛ የይግባኝ መብት አለው፡፡
4. በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ 1064/2010 እና በዚህ መመሪያ በሁለቱም የሚያስቀጣ ጥፋት የተፈጸመ እንደሆነ ጉዳዩ በመጀመሪያ በቀረበበት ህግ መሠረት ይታያል፡፡

**አንቀጽ 24. የዲስፒሊን ኮሚቴ ስልጣን፤**

የዲስፒሊን ኮሚቴው ስልጣን በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 እና በዲስፒሊን አፈጻጸም የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 77/94 በተሠጠው ስልጣን መሠረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 25. ስለይርጋ**

ማንኛውም የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኛ የሥነ-ምግባር መመሪያውን በመተላለፍ የስነ-ምግባር ግድፈት ወይም ጥፋት ከፈፀመ ክሱ የሚቀርብበት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 73 ከንዑስ አንቀጽ /1/- /5/ መሠረት ይሆናል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>፡- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 26. ጥቆማን ስለማሳወቅ**

1. ማንኛውም የአካዳሚክ ዘርፍ ሠራተኛና ኃላፊ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱ መርሆችን የሚፃረር የስነ-ምግባር ጉድለት መፈፀሙን በማንኛውም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል፣ከበድ ያለ ከሆነም ለኮሚሽኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. የሚያቀርበው ጥቆማ እውነተኛ፣ያልተዛባ፣ከበቀል የፀዳ፣አሳሳች ያልሆነና ምክንያታዊ በሆነ እምነት የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡ጥቆማ አቅራቢው ከማንኛውም የበቀል ጥቃት መጠበቅ መብት አለው፡፡

3. ጥቆማ አቅራቢው ማንነቱ እንዳይገለጽ ከፈለገ ማንነቱ በሚስጥር መያዝ አለበት፡፡

**አንቀጽ 27. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሠራተኛና ኃላፊ የስነ-ምግባር ክፍሉ ለስራው የሚፈልገውንና የሚጠይቀውን መረጃና ድጋፍ በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 28.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 29. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት በማናቸውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

*ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ 2011 ዓ/ም*